ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ
Wisdom at the source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ.-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 11፣ ታህሳስ 2008

## የአስተዳደር ሠራተኞች ልማት በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

**The Micro and Macro Contributions of Civil Society Organizations [‘*Totaw Cafe*’: Sphere of Public Debate?]**

Chalachew Tarekegne

**የሃገሩን ሰርዶ...**

በስለሺ ሰማኸኝ

**ሸኙና ተሸኘ**

በደስታ ተከስተ

**«ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው»**





የማህበረሰብ አገልግሎት ቀን በተለያዩ ዝግጅቶች በዩኒቨርሲቲው ሲከበር





ዶ/ር ማተቤ ታፈረ እና ፕሮፌሰር ዘላለም ተመስገን ኮሌጁ "update in clinical medicine: a continuing medical education and outreach program" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ ንግግር ሲያደርጉ

... ገጽ 4






የቱሪዝም ሳምንት በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሲከበር

እውነትን መፈለግና ስሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

**Core Values**

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


# ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
አቶ እምቢያለ በየነ
አቶ አማረ ካሳው
አቶ በላይነህ ወርቁ
ዶ/ር አልማዝ ጊዜው
አቶ ፈታሒ በቃሉ
ወ/ሮ መድኃኒት በላቸው
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ሂሩት አድማሱ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ቻላቸው ታረቀኝ
ስለሺ ሰማኸኝ
ደስታ ተከስተ

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ
ፋንታነሽ ላቀው

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው
አለምነሽ ሙሉ

ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# ለዩኒቨርሲቲው ግቦች ስኬት የማህበረሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ ነው!!!

በአገራችን ኢትዮጵያ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለማሳካት መሠረታዊ እመርታ ሊመዘገብባቸው ከታቀዱ ዘርፎች አንዱ የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ነው፡፡ በሀገራችን የትምህርት ፖሊሲ መሠረት ጥራት፣ አግባብነትና ተደራሽነት ያለው ትምህርትና ስልጠና መስጠት እንደ ዋነኛ ግብ ተቀምጧል፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አገራዊ ግቦችን መሠረት በማድረግ ራዕይ ጥበብ 2017ን ለማሳካት ያስቀመጣቸውን ስትራቴጅክ ግቦች በተሟላ ሁኔታ ለማሳካት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ሚና እጅግ ወሳኝ እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡ ዩኒቨርሲቲው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱን በውጤት ተኮር ስርዓት ቀርፆ 2008 ዓ.ም በመማር ማስተማር፣ በምርምር፣ በማሕበረሰብ አገልግሎት፣ በቴክኖሎጂ ስርጸት/ሽግግር እንዲሁም በመልካም አስተዳደር ዘርፎች ስራውን በስፋት እየሰራ ይገኛል፡፡ አበረታች ውጤትም እያስመዘገበ ይገኛል፡፡

በዕውቀት፣ ክህሎትና በአመለካከት ብቁ፣ ተገቢ የሆነ የሰው ኃይል የማፍራት ስራውን ማጠናከር፤ የምርምር ማዕከላትንና ቡድኖችን አሁን ካሉበት በበለጠ በማጠናከር በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ያተኮሩና ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮችን ማካሄድ፤ ዩኒቨርሲቲው መልካም አስተዳደር የሰፈነበት፣ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ስራ የሚካሄድበት እንዲሆን ማስቻል፤ የክልሉን ፍላጐት ማዕከል ያደረገ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራን በማጠናከር በማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ ፋይዳ ያላቸው የማሕበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ማከናወን የዕቅዱ መነሻዎች ናቸው፡፡

ዩኒቨርሲቲው አገሪቱ የምትፈልገውን በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት የበኩሉን አገራዊ አስተዋጽኦ ማበርከት እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ይህንንም እውን ለማድረግ በ2008 ዓ.ም ባለፉት አመታት በዩኒቨርሲቲው የተመዘገቡ መልካም አፈፃፀሞችን አጎልብቶና ክፍተቶችን በማረም ለቀጣይ ስኬት ርብርብ ለማድረግ የአመቱን ግቦችና ዝርዝር ተግባራትን አስቀምጧል፡፡ እነዚህን ግቦች ተግባራዊ ለማድረግ የአፈፃፀም አቅጣዎችን በማስቀመጥ እንዲሁም አላማዎቹን በማህበረሰቡ ውስጥ በማስረጽ መምህራን፣ ተማሪዎችና የአስተዳደር ሠራተኞች የራሳቸውን እቅድ በማዘጋጀት ለግቡ ስኬት የራሳቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በተዋረድ ያሉት እቅዶችና ዝርዝር ተግባራት ለአጠቃላይ የዩኒቨርሲቲው አመታዊ እቅድ ስኬት ወሳኝ መሆናቸው ቀደም ባሉት ጊዜያት ከተገኘው ውጤት ተሞክሮ የተወሰደበት ጉዳይ ነው፡፡

ጠንካራ የትምህርት የልማት ሠራዊት መፍጠር የሚያስችለውን በአመራር፣ በመምህራን፣ በአስተዳደር ሠራተኞችና በተማሪዎች ደረጃ የተደራጁ አካላትን ተጨባጭና ውጤት ተኮር ተግባራትንና አደረጃጀቶችን የመደገፍ ስራ የሁሉም ድርሻ ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በ2008 ዓ.ም. የግማሽ አመት አፈጻጸም የመማር፣ መመራመርና መተግበር (የመመመ) ቡድኖችን በይበልጥ በማጠናከርና ጅምር እንቅስቃሴዎችን በማስቀጠል በዩኒቨርስቲው ውስጥ እየታዩ ያሉት የለውጥ ሥራዎች ይበልጥ እንዲጠናከሩ የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት፡፡ ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን፣ በየደረጃው ያለው አገልግሎት አሰጣጥ ዘመናዊ፣ ግልፅ ፍትሃዊነትና ብልሹ አሠራርን ለማስወገድ የሚያስችል እንዲሆን ለማድረግ የሁሉም ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡

የ2008 ዓ.ም መንፈቅ ተጠናቋል፡፡ ከዩኒቨርሲቲው ራዕይና ግቦች በመነሳት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ማለትም አመራር፣ መምህራን፣ ተማሪዎችና የአስተዳደር ሠራተኞች የራሳቸውን እቅድ በእነዚህ ስድስት ወራት ተግባራዊ መደረጋቸውን በማረጋገጥና የተመዘገቡ መልካም አፈፃፀሞችን በማጎልበት እንዲሁም ክፍተቶችን በማረም በቀጣይ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ጠንክሮ መስራት ይኖርበታል፡፡ መልካም አፈፃፀሞችን አጐልብቶና ክፍተቶችን አርሞ በቀሪዎቹ ስድስት ወራት ውስጥ በመማር ማስተማር፣ በምርምር፣ በማሕበረሰብ አገልግሎት፣ በቴክኖሎጂ ስርጸት/ሽግግር እንዲሁም በመልካም አስተዳደር ዘርፎች ዙርያ መልካም ውጤቶችን በማስመዝገብ ለዩኒቨርሲቲው ግቦች ስኬት ሁሉም ጠንክሮ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም የእቅዶቹ ስኬታማነት የሚወስነው በእያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የላቀ ተሳታፊነት ነውና!

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

በናይል ጋዜጣ ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

## ቁልፍ መልዕክት

# የአስተዳደር ሠራተኞች ልማት በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ዩኒቨርሲቲያችን እየተገበረ ያለውን ራዕይ ጥበብ 2017 ለማሳካት የአስተዳደር ሠራተኞች ልማት ወሳኝ መሆኑን አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት የአስተዳደር ሠራተኞች ልማት የሚተገበርበት አግባብ ላይ ዘርፈ ብዙ እሳቤዎችን ለማየት ተሞክሯል፡፡ ይህ አጭር ጽሑፍ የአስተዳደር ሠራተኞች ልማት በራዕይ ጥበብ 2017 መስመራችን እንዴት እንደሚታይ በአጭሩ በመግለጽ በተከታታይ ውይይት የሚዳብርበትን አግባብ ለመፍጠር ነው፡፡

የዩኒቨርሲቲያችንዋነኛተልዕኮዎች መማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሳኩ የአስተዳደር ሠራተኞች የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ ይህን ቁልፍ ሚና እንዲጫወቱ በአመለካከት፣ በዕውቀትና በክህሎት ሊገነቡ ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት በራዕይ ጥበብ 2017 የአስተዳደር ሠራተኞች ልማት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ሠራተኞች በስራ ላይ ስልጠና፣ በአጫጭር የሀገር ውስጥና ውጭ ሀገር ስልጠናና በረጅም ጊዜ ስልጠና እንዲገነባ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

በስራ ላይ ስልጠና የሚባለው አንድ ልምድ የሌላትን/የሌለውን ሠራተኛ ልምድ ካከበተች ሠራተኛ ጋር እንዲሠራ በማድረግ በተግባር ስምሪት አቅም እንዲገነቡ የማድረግ ሂደት ነው፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ልምድ የሌለው አናፂ ልምድ ካለው አናፂ፣ አንድ ልምድ የሌላት የግዥ ሠራተኛ ልምድ ካለው የግዥ ሠራተኛ፣ አንድ ልምድ የሌለው አካውንታት ልምድ ካለው አካውንታት ወዘተ. መማር ማለታችን ነው፡፡ ይህን ተግባር መሰረት ያደረገ ስልጠና እጅግ በጣም ጠቃሚና ሊለካ የሚችል ነው፡፡ ሰራተኞቻችንም በቀላሉ እንዲያድጉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረጉም በላይ በራስ የመተማመንና ደስተኛ መሆንን ያጐናጽፋቸዋል፡፡ ይህ የስልጠና ዘዴ ውጤታማ እንዲሆን ልምዱን ለማካፈል ቀናይ የሆነ/ችና ከሌሎች ለመማር የተዘጋጀ አስተሳሰብ በጥንድ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል፡፡

ሁለተኛው የአስተዳደር ሠራተኞችን የምናበቃበት የራዕይ ጥበብ 2017 መስመር አጫጭርና ከስራው ጋር የተዛመዱ ስልጠናዎችን በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ እንዲሰለጥኑ ማድረግ ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲያችን ልንሰጠው የማንችለውን ስልጠና በሀገራችን በሌሎች ተቋማት ወይም ውጭ ሀገር ልከን የምናሰለጥንበት አግባብ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መምህራንን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ለአጫጭር ስልጠና እንደምንልክ ሁሉ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችንም በዚህ አግባብ ማስተናገድን ያቀፈ ነው፡፡ ግልጽ አሠራር በፍጥነት በመዘርጋት ሊተገበር የሚችለውን የውጭ ሀገር ስልጠና እስከአሁን ያልተጠቀምነበት መስመር ነው፡፡ አጫጭር ስልጠናዎች መመዘን ያለባቸው በሠራተኞች ላይ በሚያመጡት ግንዛቤ፣ ዝንባሌና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡

ሶስተኛው የአስተዳደር ሠራተኞች የምናበቃበት የራዕይ ጥበብ 2017 መስመር የረጅም ስልጠና ዘዴ ነው፡፡ ይህ አሠራር ሠራተኞች በተሰማሩበት ዘርፍ የማሳደግ ዕድላቸውን ለማስፋትና ዩኒቨርሲቲውንም አቅማቸው በከፍተኛ ደረጃ በተገነቡ ሠራተኞች እንዲመሰረት ለማድረግ አልሞ የሚተገበር ፕሮግራም ነው፡፡ የአስተዳደር ሠራተኞች እንደ መምህራን በተከታታይ አቅማቸውን በማሳደግና በአፈፃፀምም ውጤታማ በመሆን ማደግ እንችላለን የሚሉ እሳቤዎች እንዲኖራቸው ማድረግ እንደሚገባ በራዕይ ጥበብ 2017 ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት የፕሮግራም አመራረጣችን መሻሻል የሚኖርበት ቢሆንም ለአስተዳደር ሠራተኞች መጠነ ሰፊ የረጅም ጊዜ የስልጠና ዕድል ተሰጧል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ወደፊትም ይህን ስራ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ የዩኒቨርሲቲው መገለጫዎች መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞችና ተማሪዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም አንድ ትልቅ መገለጫ የሆኑትን የአስተዳደር ሠራተኞች በተከታታይ የማልማት ሂደት ወሳኝ ስራችን ነው፡፡ ከላይ ከተገለፁት ከስራ ጋር ከተቆራኙት ስልጠናዎች በተጨማሪ የሀገራቸውን የተለያዩ ገጽታዎች እንዲያዩና ሀገራዊ ዕውቀታቸውን እንዲዳብር ማድረግና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስልጠናም መስጠት ተገቢ ስራዎች ናቸው፡፡

ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!

# አበይት ዜናዎች...

## ሁለተኛው የቱሪዝም ሳምንት ተከበረ

በየማነ ገብሩ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቱሪዝምና ሆቴል ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ከአማራ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ ከባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት መምሪያ፣ በክልሉ የዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ፣ ከቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በመተባበር የሁነቶች ቱሪዝም ከሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪ ጋር መስራት ያለው ግንባር ቀደም ሚና (MICE tourism at front line of working with the hospitality industry) በሚል መሪ ቃል የቱሪዝም ሳምንትን በተለያዩ ዝግጅቶች አከበረ፡፡

የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ዲን አቶ በላይነው አስሬ በአውደ ርዕዩ ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ አስተላልፈው ባህል የአንድ ማህበረሰብ ንብረትና የእለት ተእለት የህይወት ጉዞ መገለጫና ማንነት በመሆኑ ይህንን ውድና ድንቅ የህዝብ ሀብት ይዘቱን ሳይለቅ በተደራጀ መልክ በጥናትና በምርምር በመታገዝ ለአለም ህዝቦች እንዲያውቁ ማድረግና ወደገቢ ምንጭ በመቀየር ለማህበረሰቡ ብሎም ለሀገሪቱ በሚጠቅም መልኩ በመከወን ዙርያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተግባር ጉልህ ድርሻ እንዳለው ተናግረዋል፡፡ ይህ የቱሪዝም ሳምንት ሲከበር መምህራን ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጡት ትምህርት ከጽንሰ ሃሳብ በዘለለ ወደ ተግባር ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት በመቀየር ተማሪዎቻቸው ከእለት ተእለት ተግባራቸውን በመማር ከዘመኑ የሚራመድ እውቀት ይዘው እንዲወጡ በማድረግ ዙሪያ ጉልህ ሚና ይኖረዋል ብለዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው በክልሉ ውስጥ ያሉት የተፈጥሮ ሀብት፣ ቁሳዊና ማህበራዊ እሴቶችና የቱሪስት ማዕከላት በምርምር መለየትና ማወቅ እንዲሁም የተገኙ የምርምር ማዕከላት ምቹ ለማድረግ ስርዓት መዘርጋትና የተሟላ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ማዘጋጀት በቱሪዝም ኢንዱስትሪ እድገት ላይ የጎላ አስተዋጽኦ እንዳለው ተናግረዋል፡፡ ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው ለዚህ ስርዓት የሚዘረጉ፣ የሚተረጎሙና በእውቀት ላይ የተመሰረተ አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች ለማፍራት የመማር ማስተማር ሂደቱ በተግባር የተደገፈ ትምህርት መስጠት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡ ዶ/ር ተስፋዬ አክለው እንደተናገሩት የክልላችን መዲና ባሕር ዳር ከጊዜ ወደ ጊዜ የቱሪስቶች አይን ማረፊያና የተለያዩ አለም አቀፍ የስብሰባ ማዕከል እየሆነች ያለችበት ወቅት በመሆኑ ለእነዚህ ጎብኝዎች የቆይታ ጊዜያቸውን የሚያራዝሙበት ተገቢ መስተንግዶ መስጠት የሚችል ባለሙያ ማፍራት አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

የአውደ ጥናቱ ዋና አላማ የMICE TOURISM (የሁነቶች ቱሪዝም ሆስፒታሊቲይ ኢንዱስትሪ) ምንነትና ጠቀሜታው በተማሪዎችና በማህበረሰቡ ማስረጽ እና ተማሪዎች ከሚያገኙት እውቀት ነገ እራሳቸውን በተግባር መተርጎም የሚያስችል ክህሎት ማስጨበጥ ነው፡፡ የቱሪዝም ሳምንቱ ለተከታታይ 5 ቀናት በጥናታዊ ፁሑፍ፣ በዓውደ ርዕይ፣ የእግር ጉዞ፣ ባህላዊ ትርኢትና የተለያዩ አልባሳትን በመጠቀም በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል፡፡

## የህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አውደ ጥናት አካሄደ

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አሜሪካ አገር ከሚገኘው ማዮክሊኒክ ጋር በመተባበር "update in clinical medicine: a continuing medical education and outreach program" በሚል ርዕሰ ጉዳይ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት አዳራሽ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

አውደ ጥናቱን በንግግር የከፈቱት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ ጥሪ ለተደረገላቸው እንግዶችና ከሀገር ውጭም ሆነ ከሀገር ውስጥ ለመጡ ታዳሚዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው ዩኒቨርሲቲው የጥበብ አምባ እንደመሆኑ መጠን የ2017ን ራዕይ ለማሳካት የተለያዩ አኩሪ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በህክምናው ዘርፍ ጠንክሮ እየሠራ እንደሚገኝ ጠቁመው አውደ ጥናቱ በህክምናው ዘርፍ በምርምር እና በስራ ዓለም ላይ ለተሰማሩ የጤና ባለሙያዎች እንዲሁም ለተማሪዎች የማንቂያ ደወል በመሆን ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

የኮሌጁ ዲን ዶ/ር ጌታቸው ሙሉቀን ከማዮክሊኒክ ጋር በመተባበር የሚሰራው ስራ የኮሌጁን ተማሪዎች ከማብቃት ባሻገር የክልሉን የጤና ዘርፍ አቅም በመገንባት እንዲሁም ሳይንስና ቴክኖሎጂ የደረሰበትን ደረጃ ለማወቅ ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ገልፀዋል፡፡ ዶ/ር ጌታቸው አያይዘውም የአውደ ጥናቱ ዋና ዓላማ በተለይ በታዳጊ ሀገር ላይ የሚከሰተውን ተላላፊ በሽታ ለይቶ በማውጣት ከአሜሪካ ከመጡ ታዋቂ ሀኪሞች የልምድ ልውውጥ በማድረግ ሀገራችን ላይ ያሉ የጤና ባለሙያዎችን አቅም መገንባት ነው፡፡

የማዮክሊኒክ ባልደረባ ፕሮፌሰር ዘላለም ተመስገን በህክምናው ዘርፍ የሚማር ባለሙያ 25 በመቶ ከትምህርት የሚያገኝ ሲሆን ቀሪውን 75 በመቶ ግን በተግባር ወደ ሥራው ሲሰማራ የሚቀስመው እውቀት እንደሆነ ገልጸው በሀገራችን ያሉ የጤና ተቋማት ምንም እንኳ የተሟላ የህክምና መሣሪያ ባይኖራቸውም ባለው ለመጠቀም እና የተለያዩ አማራጮችን ለመውሰድ በአውደ ጥናቱ ላይ የሚቀርቡት ጥናታዊ ፅሁፎች ከፍተኛ የእውቀት ሽግግር እንደሚያበረክቱ ተናግረዋል፡፡

በሀገራችን ያሉ የበሽታ ዓይነቶችን በምን ዓይነት መልኩ መፍትሔ መስጠት እንደሚቻል፣ ማንኛውንም በሽታ ለመለየት በመሳሪያና በምርምር የተደገፈ ውጤት እንደሚያስፈልግ በምክክር መድረኩ ከቀረቡት የምርምር ውጤቶች መገንዘብ እንደቻሉና ለወደፊት በዘመናዊ የህክምና ዘዴ ለመስራት ያገኙት የልምድ ልውውጥ ከፍተኛ መሆኑን ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡

## ማዕከሉ የአሳ ምርትን ለማሳደግ የሚካሄደውን ምርምር ለማገዝ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ተገለጸ

በታድዬ አስማረ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ማዕከል ያደረገና በሀገር አቀፍ ደረጃ ሞዴል የሚሆን የአሳ ግብርና ልማት ሁለገብ ማዕከል በባሕር ዳር ከተማ ጣና ሐይቅ አካባቢ ለማቋቋም ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ማዕከላት የተውጣጡ የዘርፉ ባለሙያዎች ምክክር አካሄዱ፡፡ የምክክር መድረኩ የአሳ ግብርና ልማት ዘርፍ ማዕከልን በማቋቋም የአሳ ምርትን በምርምር በተደገፈ ዘመናዊ አሰራር የሚያስችል ሲሆን ማዕከሉ የአሳ ምርትን ለማሳደግ የሚካሄደውን ምርምር ለማገዝ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር እያዩ ሞላ የዓሳ ግብርና ልማት ምሁራን የአሳ ግብርና ልማት እንቅስቃሴ አነስተኛ መሆን አሳስቧቸው ዘርፉን ለማሳደግ ትኩረት ሰጠው የምክክር መድረኩን ማዘጋጀታቸው ለማዕከሉ እውን መሆን ያላቸውን ቁርጠኝነት እንደሚያሳይ ገልጸው የውሃ ሀብታችንን ከመስኖ እና ከሀይል ምንጭ በተጨማሪ አሳ ግብርና ልማት ማዕከላትን በማቋቋም ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሳተፉ በማድረግ ዘርፉን ማሳደግ አለብን ብለዋል፡፡

በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂክ ከእንስሳት ሀብት በተጨማሪ የአሳ ግብርና ልማት ኢኮኖሚውን እንደሚደግፉ መንግስት አምኖበት በሚኒስተር ደረጃ የእንስሳትና አሳ ልማት ሚኒስቴር ሲቋቋም የአሳ ሀብት ልማት ራሱን ችሎ በሚኒስተር ዴኤታ እንዲመራ በማድረግ ለክልሎች ድጋፍ በማድረግ ዘርፉ እንዲያድግ እያደረገ እንደሚገኝ የገለጹት ዶ/ር እያዩ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት ለሠጠው የአሳ ግብርና ልማት ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም ማዕከሉ በባሕር ዳር እንዲቋቋም ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ወደፊትም በዘርፉ ለሚካሄዱ ምርምሮች ከተመራማሪዎች ጎን በመሆን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል፡፡

በመድረኩ በኢትዮጵያ በአሳ ልማት ዘርፉ እየሠሩ የሚገኙ ማዕከላትና የምርምር ተቋማት የተገኙ ሲሆን በሥራ ሂደት ያጋጠሟቸውን መልካም አጋጣሚዎች እና ተግዳሮቶች እንዲሁም የተወሰዱ መፍትሄዎችን ቀርበዋል፡፡ ማዕከሉን በቴክኒክና በገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግ ዓለም አቀፍና ሀገር በቀል ተቋማትን በመለየት ማዕከሉ እውን እንዲሆን የሚያደርግ አብይ ኮሚቴ የተሰየመ ሲሆን በአሳ ልማት ላይ የተካሄዱ የተለያዩ የምርምር ሥራዎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

## የጎርፍ አደጋን ለመከላከል የሚያስችል የተግባር ስልጠና ተሰጠ

በአምሳሉ ጥላሁን

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጥናት ተቋም የጎርፍ አደጋ ለመከላከል የሚያስችል የተግባር ስልጠና ለባለሙያዎች ሰጠ፡፡ የስልጠናው ዋና አላማ በክልሉም ሆነ በሀገሪቱ ላይ የሚከሰተውን የጎርፍ አደጋ እንዴት መቋቋም እንደሚቻልና ህዝቡ ላይ አስከፊ አደጋ እንዳይደርስ አስቀድሞ ለመከላከል፣ የጎርፍ አደጋው ከተከሰተ በኋላ የተግባቦት፣ የማስተባበር እና የንብረት አስተዳደር ምን መምሰል እንዳለበት በተግባር ለማሳየት ነው፡፡

በስልጠናው ላይ ተገኝተው የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጥናት ተቋም ኃላፊ ዶ/ር ደረጀ ፀጋዬ ሲሆኑ ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት ተፈጥሯዊ አደጋዎች የሚፈራረቁባት አገር እንደሆነችና በተለይም በአየር ለውጥ የሚከሰቱ አደጋዎች በተለይም ድርቅና ጎርፍ ዋነኛ ተጠቃሾች እንደሆኑና እነዚህ ክስተቶች በህዝቡና በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ተጽዕኖ እያሳደሩ ስለሚገኙ ይህን ጉዳት ለማስቀረት መንግስትም ሆነ ህዝቡ ቁርጠኛ ውሳኔ መውሰድ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

ተቋሙ የተቋቋመበት ተልዕኮና ራዕይ ጥራት ያለው ትምህርት፣ ምርምር፣ ማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት እንደሆነ ዶ/ር ደረጀ ጠቁመው በአሁኑ ጊዜ ለማህበረሰቡ ስልጠና፣ ጥናትና ምርምር እንዲሁም ለፖሊሲ አውጭዎች፣ ተግባሪዎች እና ውሳኔ ሰጭዎች የሚያግዝ ሥራ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ አማረ ክንዴ በስልጠናው ላይ እንደተናገሩት የጎርፍ አደጋን ለመከላከል የፌደራሉ መንግስትም ሆነ የክልሉ መንግስት ዘርፍ ብዙ ሥራዎች በመጀመሪያው የትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂክ እቅድ ሲሠሩ እንደቆዩና አሁንም

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# አበይት ዜናዎች...

## ዩኒቨርሲቲው ያሰለጠናቸውን የተማሪ ፖሊሶች አስመረቀ

**በሙሉጎጃም ዓንዱአለም**

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከ2ኛ ፖሊስ ጣቢያ ጋር በመተባበር ለተከታታይ አስር ቀናት ያሰለጠናቸውን መቶ የተማሪ ትራፊክ ፖሊሶች በዩኒቨርሲቲው የመሰብሰቢ አዳራሽ አስመረቀ፡፡

በምርቃት ስነ ስርአቱ ላይ የተገኙት የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው በሀገራችን ስላልተለመደ እንጂ በውጪው አለም ታዳጊ ህፃናት ከፖሊስ ጎን በመሰለፍ የአካባቢን ደህንነት ሲጠብቁ እንደሚስተዋሉ አስገንዝበው ተመራቂዎቹ ለወደፊት በከተማው ላይ የሚከሰተውን የትራፊክ አደጋን ለመከላከል የጀርባ አጥንት በመሆን ባሕር ዳርን ወጥ የሆነ የትራፊክ ደህንነት የሚስተዋልበት ከተማ ለማደረግ እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡

የእለቱ የክብር እንግዳና የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ ምክትል ኮማንደር ውበቱ አለ የትራፊክ አደጋ ችግር ከእለት ወደ እለት እየተስፋፋና መሻሻል ያልታየበት ስለሆነ ተመራቂዎች ከቤተሰቦቻቸው ጀምረው ለትምህርት ቤት ጓደኞቻቸውና ለመላው ህብረተሰብ ግንዛቤ በማስጨበጥ ለውጥ ለማምጣት ጠንክረው እንዲሠሩ አሳስበዋል፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለስልጠናው መሳካት የአንበሳውን ድርሻ የወሰደ በመሆኑና ከአሁን በፊትም በርካታ ሥራዎችን በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ስላበረከተ ከፍ ያለ ምስጋና አቅርበው ለወደፊቱም ከጎናቸው እንደሚሰለፍ ያላቸውን ተስፋ ገልፀዋል፡፡

ምክትል ኢንስፔክተር መታከት ፈረደ የ2ኛ ፖሊስ ጣቢያ የመንገድ ደህንነት ትራፊክ ክፍል ኃላፊ ስልጠናውን በዋናነት ሲከታተሉ የቆዩ በመሆናቸው የስልጠናውን ዋና ዓላማና አስፈላጊነት የሚገልፅ ሪፖርት አቅርበዋል፡፡ ከቀረበው ሪፖርት ለመረዳት እንደተቻለው የሰለጠኑት ተማሪዎች ከሹምአቦ እና ከድልችቦ ትምህርት ቤቶች ከ4-8ኛ ክፍል ካሉት መካከል የተውጣጡ እንደሆኑና ከአለም አቀፍ ተሞክሮ አንፃር በእድሜ ታናናሽ ህፃናቶች በክበብ ታቅፈው እንዲቆዩ እንዲሁም ከፍ ያሉት ደግሞ በተግባር ሥራ ላይ የሚሠማሩ ተብለው በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ትምህርቱን በሚገባ ወስደው ለምረቃ በቅተዋል፡፡

በምረቃው ስነ ስርዓት ላይ በአጠቃላይ አፈፃፀም ያላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ሁለት ወንዶችና አንድ ሴት ተማሪዎች ከክብር እንግዳው ምክትል ኮማንደር ውበቱ እና ከምክትል ፕሬዚዳንቱ ዶ/ር ተስፋዬ እጅ ሽልማት ተሰጥቷቸዋል፡፡ በስልጠናው ወቅት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱት ግለሰቦችና ተቋማት ዩኒቨርሲቲውን ጨምሮ የምስክር ወረቀትና የተለያዩ ስጦታዎች ተበርክቷል፡፡

በምረቃው ወቅት ተማሪዎች በተግባር የተማሩትን የሰልፍ ትርኢትና የእያንዳንዱን የትራፊክ ህግ ምልክቶችን ከአሰልጣኙ የባሕር ዳር ፖሊስ መምሪያ የህዝብ ግንኙነት ዋና የሥራ ሂደት ኃላፊ ኢንስፔክተር ታደሰ ዳኛቸው በሚሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት በሚገባ አሳይተዋል፡፡

## የነጭ ሪቫን ቀን ተከበረ

**በሙሉጎጃም አንዱዓለም**

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት በአለም አቀፍ ደረጃ ለ23ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ18ኛ ጊዜ የነጭ ሪቫን ቀንን ‹‹በወንዶች አጋርነት ጾታዊ ጥቃትን በጋራ እንከላከል›› በሚል መሪ ቃል በዩኒቨርሲቲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተከበረ፡፡

መረኃ ግብሩን በንግግር የከፈቱት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት አማካሪ አቶ በቃሉ ዳዊት ሴቶች ያለምንም ጥቃትና ስጋት በነፃነት የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ ለመፍጠር ከወንዶች ከፍተኛ ኃላፊነት እንደሚጠበቅና ለወደፊት ማንኛውንም ጥቃት በጋራ መከላከል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

የስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር አልማዝ ጊዜው የነጭ ሪቫን ቀን ታሪካዊ አመጣጥ እና ጾታዊ ትንኮሳን ወይም ጥቃትን ለመከላከል በወጣው መመሪያ ላይ ሰፊ ገለፃ ያቀረቡ ሲሆን መመሪያው እንደየጥቃቱ ዓይነትና መጠን የሚወሰደው እርምጃም እንደሚለያይና ከቃላት ዘለፋ ጀምሮ ጥፋት ላደረሰው አካል ቅጣት እንደሚያስከትል ገልፀዋል፡፡ ዶ/ር አልማዝ አያይዘውም ጾታዊ ትንኮሳ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው እንደመሆኑ መጠን የተባበሩት መንግስታት እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከህዳር 25 ቀን 1999 ጀምሮ በጭቆና ቀንበር ውስጥ ለሚኖሩ ሴቶች ሁሉ በፍጥነት የነፃነት የክብርና የመነቃቃት ምልክት ይሆን ዘንድ የነጭ ሪቫን ቀን ዓለም ዓቀፍ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የማስወገድ ቀን ሆኖ እንዲከበር እውቅና መስጠቱን አስገንዝበዋል፡፡

የስርዓተ ፆታ ልማት ትምህርት ክፍል መምህር ረዳት ፕሮፌሰር ዮሐንስ መርሻ ጥናታዊ ፅሑፍ ያቀረቡ የዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣ የአስተዳደር ሠራተኞች መምህራንና ከሁሉም ግቢዎች የተውጣጡ ተማሪዎች በመረኃ ግብሩ ላይ ተሳትፈዋል፡፡ ጾታዊ ጥቃትን በአንፃራዊ ሁኔታ ለመቅረፍ በየግቢዎች ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጥና ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ማንኛውም ሰው አስተማሪ የሆነ ቅጣት እንዲሰጠው ከተሳተፊዎች ሀሳብ የቀረበ ሲሆን በተሳታፊዎች በተነሱት ጥያቄዎችና ሃሳቦች ላይ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡

## ማዕከሉ የሥራ ፈጠራ አውደ ጥናት አካሄደ

**በትዕግስት ዳዊት**

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢንተርፕርነርሽፕ ማበልፀጊያ ማዕከል ከእስራኤል ቴክኖሎጂ ሽግግር ቡድን ጋር በመተባበር በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነ የሥራ ፈጠራ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

የማዕከሉ ዳይሬክተር ወ/ሮ አለምፍሬ ደረሰ ኢንተርፕረነሮችን ከእስራኤል ቴክኖሎጂ ሽግግር ቡድን ጋር በመሆን ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ገልጸው ሃሳባቸው መሬት ወርዶ ትልቅ ተቋም እስከሚሆን ድረስ ማዕከሉ የማማከር ሙያ እገዛ እንደሚያደርግላቸው ተናግረዋል፡፡ የአውደ ጥናቱ አላማዎች ትልቅ የቢዝነስ ራዕይ ያላቸዉ ሰዎችን ማገናኘትና የልምድ ልዉዉጥ እንዲያደርጉ ማመቻቸት፣ የተሳታፊዎች የቢዝነስ ሀሳብ የሚፈታዉ ችግር/የገቢያ ፍላጎት ምን እንደሆነ እንዲለዩ ማገዝና ማማከር፣ የሚነሱ የቢዝነስ ሀሳቦች በገበያ ዉስጥ ያላቸዉን ተፈላጊነት ደንበኞችን በማነጋገር ለመለየት እንዲችሉ ማማከርና ማገዝ እንዲሁም የቢዝነስ ሀሳቦች ልምድ ላላቸዉ ባለሀብቶች እና የተሳካላቸዉ ስራ ፈጣሪዎች በማቅረብ ሙያዊ አስተያየት እንዲያገኙ ማድረግ እንደሆኑ ወ/ሮ አለምፍሬ ገልጸዋል፡፡

የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው በመክፈቻ ንግግራቸው የኢንተርፕርነርሽፕ ማዕከሉ እየሠራ ያለውን ተግባራት ዘርዝረው ለሚያሸንፉ የሥራ ፈጣሪዎች ማዕከሉ የማማከር፣ ሙያዊ ድጋፍና ሃሳባቸው መሬት ወርዶ እስከሚሠራ ድረስ በማገዝ ብቁ ሥራ ፈጣሪዎች እንደሚያደርጋቸውና በቀጣይ አመታት ለውጥ እንደሚታይ ጠቁመዋል፡፡

ለአሸናፊዎች ሰርተፍኬት የሰጡት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ እና በእስራኤል የኢትዮጵያ አምባሳደር አምባሳደር በላይነሽ ዘቫድያ ሲሆን አምባሳደር በላይነሽ ለተሳታፊዎች የራሳቸውን የህይወት ልምዳቸውን አካፍለዋል፡፡ አምባሳደር በላይነሽ አክለውም ተወዳዳሪዎች ጠንካራ በመሆን የተገኘውን ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው የፈጠራ ስራቸውን እውን እንዲያደርጉ አደራ በማለት አውደ ጥናቱ መካሄዱ በኢትዮጵያ እና በእስራኤል መካከል ያለውን ግንኙነትም ያጠናክራል ብለዋል፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ ከሃያ ሰባት የሥራ ፈጠራ ሃሳቦች የተመረጡት አስሩ በእስራኤል ቴክኖሎጂ ሽግግር ቡድን ዳኞች እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ኢንተርፕረነሮች ተገምግመው ለውድድር ቀርበዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ አውደጥናቱ መረጃ እና ልምድ እንደተገኘበት ገልጸው የፈጠራ ሙያና ተሠጥኦ ያላቸውን ሰዎች ሃሳባቸውን ወደ ተግባር በመቀየር ውጤታማ እንዲሆኑ አደራ ብለዋል፡፡

## የማህበረሰብ አገልግሎት ቀን በተለያዩ ዝግጅቶች ተከበረ

**በትዕግስት ዳዊት**

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ቀን በተለያዩ ዝግጅቶች ተከበረ፡ ፡ በእለቱ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው የምርምር ዳይሬክተር ዶ/ር ዋሴ አንተነህ ዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራውን በተደራጀ መልኩ እየሠሩ መሆኑን ገልፀው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብም ትኩረት መስጠት እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር ዶ/ር ጌታቸው ፍስሐ ማህበረሰቡና አጋር አካላት በማህበረሰብ አገልግሎት ላይ ላደረጉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ምስጋና በማቅረብ ዩኒቨርሲቲው በማህበረሰብ አገልግሎት እንቅስቃሴ ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም ባሉት አመታት ያከናወናቸውን ዝርዝር ተግባራት በማቅረብ ከተሳታፊዎች ጋር ውይይት ተካሂዷል፡፡ በውይይቱ ወቅት ተሳታፊዎች በማህበረሰብ አገልግሎት ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችንና የመፍትሄ ሃሳቦችን አቅርበዋል፡፡

በእለቱ የባሕር ዳር ከተማ የቱሪስት ካርታ ይፋ ሆኗል፡፡ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት በጂኦስፔሻል ማዕከል በአቶ ብርሃኑ ገድፍ እንዲሁም የተለያዩ አካላት ተሳትፎ እና ትብብር ተሠርቶ የቀረበው ካርታ ከ180,000 ብር በላይ እንደፈጀ ታውቋል፡፡ አቶ ብርሃኑ እንደተናገሩት የባሕር ዳር ከተማ የቱሪስት ካርታ ወደ አፕልኬሽን ሶፍተዌር በማስገባት ቱሪስት በዚህ ካርታ በመጠቀም ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጣ ተናግረዋል፡፡

የባሕር ዳር ከተማ የባሕልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ አቶ ስንታየሁ ከተማ በካርታው መዘጋጀት የተሰማቸውን ደስታ ገልጸው የቱሪስት ካርታውን ሥራ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኃላፊነት ወስዶ በመስራቱ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡ አቶ ስንታየሁ አክለውም ወደፊት በሞባይል አፕልኬሽን ላይ በመጫን ሁሉም ቱሪስቶች እንደሚገለገሉበት ተናግረዋል፡፡

በመጨረሻም በቱሪስት ካርታው እንዲሁም በሌሎች ማህበረሰብ አገልግሎት ላይ ለተሳታፉ ግለሠቦች እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲው ጋር በማህበረሰብ አገልግሎት አጋር ለሆኑ ድርጅቶች የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

## My Reflection

# The Micro and Macro Contributions of Civil Society Organizations

# [‘*Totaw Cafe’*: Sphere of Public Debate?]

**Chalachew Tarekegne (PhD Candidate)**

**Department of Civics and Ethical Studies**

It is widely acknowledged that the reappearance of civil society organizations (CSOs) has historically marshaled into the beginning of democracy; and particularly, spheres of wider public debate. In fact, it is stated, to a large extent, our conceptualization and evaluation of civil society depends on ourvisualization of democracy, public discourses and deliberations. The reverse also holds true. For some writers, democratic political theory privileges civil society because it assumes that the existence of democracy is inseparably bound up with that of civil society.

It is still important to note that the increasing labeling of civil society as Non-Governmental Organizations (NGOs) and vice-versa needs to be carefully examined. There are writers who labelNGOs and civil society organizations as potential partner groups. Nevertheless, this understanding of civil society organizations reflects the continued acceptance of a universalistic view of civil society. When civil society is referred to as “*sphere of public debate*; however, its meaning goes beyond the tantamount treatment with that of NGOs it receives.

The aim of this article is to introduce to the research community of BDU and stakeholders so that renewed attention is given to civil society organizations by researchers, policy makers and the Ethiopian society at large. This is, mainly; because, civil society organizations have numerous advantages to foster social, political, and economic development through peaceful deliberation, negotiation, and critical discourses.

Given the importance that donors and NGOs attach to the concept of civil society, it matters a great deal that NGOs should not mix-up into the divide over the meaning of civil society, particularly where societies are heterogeneous. The ways in which NGOs perceive civil society and consequently plan development projects to facilitate the work of civil associations, can have a significant effect on the extent of devolution of civil society in a country like Ethiopia. Though the focus is not to deal with the debates between CSOs and NGOs, for the time being, it is recommended that the NGOs should better try to explore the full theoretical implications of civil society organization and clearly articulate their own interpretations of its nuances.

It is clear that the current era of globalization has brought general retreat from centralized governance, and has shifted focus from a centralized ; for instance, Ethiopian state to a decentralized local institutions. This does not mean; however, large-scale globalization hasdissolved nation-states like the Ethiopian state. Still this does not mean, it does not have repercussions on our collective identity. Truly, our collective identity has lost its previous position of overwhelming primacy; and because of world politics.

In the 21st century, it is also asserted , world politics is also being deeply shaped by sub-state solidarities like ethno-nations and by non-territorial, trans-border communities based on class, gender, race, ethnicity and religion. Undeniably, world politics has shaped our thinking of community as geographical construct based on parameters stated earlier which weakens our thinking of community. Surprisingly, however, local civil society organizations (*edirs and ekubs*) and workplace canteens like *Totaw cafe* and others in the university are contributing much more for the revitalization of our thinking of community as a virtual space of shared social, cultural and moral affinities that express that ethics of self-governance. Genuinely, the writer observed discussions, discourses, and civilized deliberations which focus on fairness, rights-based, toleration ,bargaining based on logical reasoning and mutual understanding among faculty members (usually sitting together in circles). Sometimes, it is also observed, discussions related to professional mentoring and coaching kind of approaches which are very essential to shape the daily institutional practices (curriculum design, teaching-learning, assessment, research and community services) in each sphere of faculty professionals regardless of the differences among groups. The topics subjected to discussions cover wide range of issues which are numerous to enlist them.

***Yet, these kinds of community- based institutions, however, need strong support from stakeholders in terms of professional advice and leadership qualities.***

Interestingly, local institutions like ***Totaw Cafe*** and canteens similar to it are playing ingenious attempt to tighten the earlier social bonds that existed in our thinking of ***WE*** (The Ethiopian Community). Hence, in this regard, it is possible to infer, indigenous institutions that are established with the free will and full consent of the community are demonstrating sufficient evidences of civic-engagement and social trust as has also been argued by Professor Robert Putnam in his article [*Bowling Alone: America’s Declining Social Capital”. Journal of Democracy Vol.6 ,No .1 January 1995]*. Accordingly, therefore, there appears the need to capture the informal community initiatives that are being organized by the community in any parts of the country. There are civil society organizations that emerge without government help and which are often succeeded in serving the most vulnerable sections of society where government finds difficult to reach. Owing to this fact, there is also the need to begin Resurrecting the Cultural and Moral Affinities among the Ethiopian citizens (communities) through providing spheres for public debate like that of *Totaw cafe and canteens in the university* are witnessing.

Worthily, ***Spheres of Public Debates*** created byindigenous civil society organizations like that of *Totaw cafe*, provides windows of opportunity to open space for civic engagement, academic discourses, and democratic deliberations than formally institutionalized public spheres for debate, where people, sometimes appear in them for mere existence in person; and no contribution for critical academic discourses and critical deliberations. The debates at *Totaw cafe* are *Natural*, *Real* and *Genuine* while that of debates at formalized forumsare *Imitative*and *Artificial*. Thus, this reflection would help us to rethink other spheres of public debate where professionals, peers, colleagues, local communities, business men and the media can contribute to good governance processes for *holistic human development* in particular and overall institutional performances improvement in general. Still, there is a need to conduct further research on: Why are debates natural at Totaw Cafe and Canteens in the University while they are imitative in formalized public spheres? Still there is a need to conduct further research on: Which kind of debate is relevant to maximize academic discourse in the university: Formal Debate or Informal Debate? How can we measure their impacts to make sound decisions? At regional and national level also, why are discussions/debates at formal spheres/ stages largely imitative while they are genuine, real, and natural in those civil society organizations? Is it not food for thought for proponents voicing to consolidate governance?

Thus, it seems possible to infer that the emergence and strengthening of the self-instituted civil society organizations as an autonomous social partner alongside the formal bureaucratic, political andeconomic structures of government will thoroughly improve governance systems: efficiency and effectiveness, consensus, participation, respecting law, accountability, transparency, responsiveness, equity, inclusiveness, and toleration. Yet, these kinds of community- based institutions, however, need strong support from stakeholders in terms of professional advice and leadership qualities. Indigenous local community based organizations, on the other hand, must keep in view that their influence on the process of regional, national and global governance will remain quite limited unless they succeeded in effectively channeling the government’s policy formulation and implementation. The new trends in globalization and its principles of cutting budget, deregulation, free trade, and privatization will affect them. For instance, scarcity of goods may retard their progress or their delivery of services timely.

Participatory observation at *Totaw cafe* and canteens in the university, clearly informed us that social and economic development has also to be indigenous, contextual and innovative, especially in the developing country

continued on page 13

# የሃገሩን ሰርዶ...

በስለሺ ስማኸኝ

የጋዜጠኝነትና ተግባቦት መምህር

በ2006 ዓ.ም በአንዲት ቀን በባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ የሴኔት አዳራሽ ትውልድ መቅረጫ ስርዓተ ትምህርቶች ቀርበው አንድ በአንድ እየተገመገሙ ነው፡፡ ወረፋው ለባሕል ጥናት (ፎክሎር) ስርዓተ ትምህርት ደረሰና ውይይት ተጀመረ፡፡ በውይይቱ ላይ አወዛጋቢ የነበረው ፎክሎር ትምህርት የሚሰጥበት ቋንቋ ነበር፡፡ ስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ትምህርቱ በሁለት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛና በአማርኛ) እንደሚሰጥና የትኞቹ የትምህርት አይነቶች በአማርኛ የትኞቹ ደግሞ በእንግሊዝኛ እንደሚሰጡ ተለይቷል፡፡ በሴኔት አባላቱ የተነሱት ጥያቄዎች ሲጠቃለሉ በሁለት ፈርጆች ይከፈላሉ፡፡ የመጀመሪያው ፎክሎርን የሚያክል በዋናነት አገር በቀል ዕውቀትን የሚዳስስ፣ የሚያጠናና የሚተነትን የትምህርት መስክ እንዴት በውጭ ቋንቋ ይሰጣል? የሚለው ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ዩኒቨርስቲዎች የፌዴራል ተቋማት ስለሆኑና ከየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል የሚመጣን ተማሪ የሚያስተናግዱ ስለሆኑ ትምህርቱ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቻ መሰጠት አለበት የሚለው ነው፡፡ ለቀረቡት መከራከሪያዎች መልስ የሰጡት የመስኩ ባለሙያዎች ያቀረቡት ማስረጃ የአንድን አገር ወይም አካባቢ ባሕል፣ እሳቤ፣ ስነ ጽሑፍ፣ ስነ ቃል፣ ስነ ግጥም፣ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ ወዘተ. ለማስተማርና ለማጥናት በማሕበረሰቡ ቋንቋ መገልገል አማራጭ የሌለው እንደሆነ ማስረጃዎችን በማቅረብ አስረግጠው እንደ አስፈላጊነቱም በሃገራችን ባሉ ሌሎች ቋንቋዎች ትምህርቱ መሰጠት እንዳለበት ገልጸው የእንግሊዝኛን ቋንቋ እንደማስተማሪያ የመረጡበት ምክንያት ግን በዘርፉ የሚገኙ ማጣቀሻ መጽሐፍት 97 በመቶው በእንግሊዝኛ ቋንቋ በመሆኑ እንደሆነ አስረዱ፡፡ ይህ ለአድማጩ አስደንጋጭ እውነታ ነበር፡፡

ይህ ማስረጃ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ለማወቅ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም፡፡ በየዩኒቨርስቲዎች ቤተ-መጽሐፍት መደርደሪያዎች ሞልተው የተደረደሩትን መጻሕፍት ሄዶ መጎብኘት ይቻላል፡፡ ብዙ ተፅፈዋል በተባሉባቸውና በራሳችን ቋንቋ በሚሰጡ የትምህርት መስኮች ሳይቀር አብዛኛዎቹ ማጣቀሻዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፉ ናቸው፡፡ በአገር በቀል ቋንቋ የተፃፉ ማጣቀሻዎች ገበያ ላይ እያሉ እንኳን የሚዘነጉበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ በኛ ቋንቋዎች በማይሰጡ የትምህርት ዘርፎች ደግሞ ትልቁ ችግር የራሳችንን ዕውቀቶችና ልምዶች አክለን አለማቅረባችን ነው፡፡ ይህ የሆነው ለምንድን ነው? ምን መደረግስ አለበት? በባሕር ዳር ዩኒቨርስቲስ በጉዳዩ ዙሪያ ምን እየተሰራ ነው?

በእነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ሃሳቤን ላቅርብ፡፡ ለችግሩ መኖር ሦስት መንስኤዎችን በዋናነት ማንሳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የትምህርት ስርዓታችን የሌሎችን አገሮች ተሞክሮ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ ስለተነሳ ነው፡፡ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ ያሉ ስርዓተ ትምህርቶችን በወፍ በረር ብንቃኝ በጣም ብዙ የሌሎች ሃገሮች ተሞክሮዎች ተቀምጠዋል፡፡ ስለአገራችን ግን ጉልህ ተሞክሮዎች፣ ፈጠራዎች...ወዘተ ተዘለዋል፡፡

እዚህ ላይ ስለሌሎች ማወቅ ጥሩ አይደለም እያልኩ እንዳልሆነ ይያዝልኝ፡፡ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲያውም የሌሎችን ማንነት ካላወቅንና ከኛ በምን እንደሚለዩ እና እንደሚመሳሰሉ ካለየን ማንነታችንን ማወቅ የማንችል እንሆናለን፤ ወይም ከኛ ውጭ ሌላ የሌለ የሚመስለን እንሆናለን፡፡ ሆኖም ግን በመጀመሪያ የራሳችንን ይዘን ሲሆን የምንገነባው የዕውቀት ግንብ የፀና፣ የሚኖረን ማንነትም በአለት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ ገጣሚው በሁለት ስንኝ የገለጸው ሃሳብ ይህንኑ ነው፡-

ከተመኙ ሳይቀር ወንዝነት መመኘት፣
ሃገርን ሳይለቁ ሰው ሃገር መገኘት፡፡

እርግጥ ነው ይህ ችግር የኛ አገር ችግር ብቻም አይደለም፡፡ የሁሉም በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮችም ችግር ነው፡፡ በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካ፣ በእስያና በምስራቅ አውሮፓ በተደረጉ ጥናቶች በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች የትምህርት ስርዓቶች ስለሌላው ዓለም (በተለይ ስላደገው የዓለም ክፍል) አብዝተው የሚያሳውቁ፣ ስለራሳቸው ታሪክ፣ ባሕልና ማንነት ደግሞ በቂ የሚባል ይዘት የማያቀርቡና አገር በቀል እውቀት እያላቸው እንደሌላቸው የዕውቀት ጥገኞች እንደሆኑ አረጋግጠዋል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ያሉት ስርዓተ ትምህርቶች በአብዛኛው የሌሎችን ቋንቋ የሚያስተምሩ፣ የሚያስነብቡ፣ የሚያጽፉና የሚያናግሩ፤ የሌሎችን ምድራዊ አቀማመጥና የሕብረተሰብ ሳይንስ፣ የሌሎችን ታሪክና ባሕል የሚያስጠኑ መሆናቸውንም ጥናቶቹ አረጋግጠዋል፡፡

እንደአብነት የጋዜጠኝነትና ተግባቦት የትምህርት መስክን ወስደን ብናይ እንኳን ኖርደንስትረንግና ብራውን እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ከ1979 እስከ 1988 ዓ.ም አጥንተው በ1998 ባሳተሙት የምርምር ስራ ላይ በአፍሪካ ውስጥ በየዩኒቨርሲቲዎች ለነበሩ ተማሪዎች በማጣቀሻነት በየቤተመጻሕፍቱ ከቀረቡት መጽሐፍት መካከል ከ93 በመቶው በላይ በምዕራቡ የዓለም ክፍል ደራሲያን ተደርሰው የቀረቡ ሲሆኑ ከነሱ መካከል ደግሞ 69 በመቶው ከአሜሪካ ብቻ የመጡ እንደሆኑ ደርሰውበታል (የቀሩት ከ7 በመቶ ያነሱ ማጣቀሻዎችም እንደ ናይጀሪያ ከመሳሰሉት አገራት ውስጥ የታተሙ ስራዎችን የሚያመለክት ነው)፡፡ በምርምር ስራው ላይ የመጽሐፎቹ ይዘቶች ሙሉ በሙሉ የምዕራቡ ዓለም ነባራዊ ሁኔታ ላይ የተመሰረቱ እንደሆኑና የአፍሪካን አካባቢያዊ ተሞክሮዎች፣ አገር በቀል ዕውቀቶችና እሳቤዎች ፈጽመው ያላካተቱ እንደሆኑ ተገልጧል፡፡ የምርምር ስራው በማደግ ላይ ያሉ የዓለም ክፍሎችን ከዳሰሰና የየአካባቢውን ሁኔታ ከተነተነ በኋላ በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካ፣ በምስራቅ አውሮፓና በእስያ በዘርፉ የተደረሱ፣ ከአካባቢው ሁኔታ የተስማሙና ለንባብ አመቺ በሆነ መንገድ የቀረቡ ማጣቀሻዎች እንደሌሉ አስምሮበታል፡፡ አሁን ይህ ጥናት ከተካሄደ 20 አመት ሆኖታል፡፡ ሁኔታው ግን አሁንም ባለበት ላይ ነው፡፡ ምናልባትም አዲስ ጥናት ቢደረግ ካለፈው ተመሳሳይ እንደሚሆን እገምታለሁ፡፡

> በሚገርም ሁኔታ ደግሞ በበለጸጉ ሃገሮች ያሉ ስርዓተ ትምህርቶች ስለሌላው ዓለም (በተለይም በማደግ ላይ ስላለው የዓለም ክፍል) እጅግ አናሳ እንዲያውም በብዙዎቹ ምንም ያልተካተተ መሆኑ በጥናት መረጋገጡ ነው፡፡

በሚገርም ሁኔታ ደግሞ በበለጸጉ ሃገሮች ያሉ ስርዓተ ትምህርቶች ስለሌላው ዓለም (በተለይም በማደግ ላይ ስላለው የዓለም ክፍል) እጅግ አናሳ እንዲያውም በብዙዎቹ ምንም ያልተካተተ መሆኑ በጥናት መረጋገጡ ነው፡፡ ብዙዎቹ የአሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ ሃገራት ስርዓተ ትምህርቶች የሌሎችን ሃገሮች ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያላስገቡ እንደሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ላይ ከላይ ባነሳሁት ተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ (ጋዜጠኝነትና ተግባቦት) ብናይ እንኳን በዓለም በዴሞክራሲና በልማት ላይ እንደ ሞዴል የሚታዩት የኖርዲክ ሃገሮች ሳይቀር ስርዓተ ትምህርታቸው ጎጥ ተኮር እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ሼርዳል የተባለ ምሁር ባለፈው አመት (2007 ዓ.ም) በሰራው የጥናት ስራው እንዳረጋገጠው በሰለጠኑት በኖርዲክ ሃገራት ውስጥ በትምህርት ዘርፉ በመጀመያ ዲግሪ የሚያሰለጥኑ 22 ተቋማት እንዳሉ፣ ከአጠቃላይ ኮርሶች ውስጥ በአማካይ ከ2-3 ኮርሶች ብቻ አለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩሩ አብራርቷል፡፡ ይህ ሁኔታ በሌሎች የትምህርት ዘርፎችም የተለየ አይመስለኝም፡፡

ይህ የአመክንዮ ግጭት በቅርቡ እኔና ሁለት ኢትዮጵያዊ ጓደኞቼ ከአንዲት የበለጸገ አገር ዜጋ ከሆነች ሴትዮ ጋር ያደረግነው የ5 ደቂቃ የትውውቅ የቃላት ልውውጥ ይገልፀዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ ሰላምታ ከተሰጣጠን በኋላ ስለአገራችን ጠየቀችን፡፡ "አገራችን ኢትዮጵያ ትባላለች" ብዬ ስለ ኢትዮጵያ አንዳንድ ነገሮችን ላብራራ ስል ቶሎ ብላ ..."Oh..I know Ethiopia. My ex-husband has brought two children from your country, Nairobi" አለች፡፡ ይህቺ ሴት ኢትዮጵያና ኬንያ የተለያየ ህዝብ፣ ታሪክ፣ መንግስት...ያላቸው እንደሆኑ አታውቅም፡፡ ከሴትዮዋ ከተለያየን በኋላ ከጓደኞቼ ጋር በሕብረተሰብ ትምህርታችን ዓለምን በሉል መስለን የሸመደድናቸውን ሃገሮች፣ የምዕራባዊያንን የፊዚክስ፣ የሂሳብ፣ የሙዚቃ ጠበብቶች፣ በአንደኛውና በሁለተኛው የአለም ጦርነት የሆነውን እያንዳንዱን...አስታወስን፡፡ ስለሌላው ዓለም የተማርነውን ያህል ስለሃገራችን የተማርነውን ሳስበው ግን ኢምንት ሆነብኝ፡፡ ስለሆነም ስለሌሎች ማወቃችን ባይከፋም ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ ያስፈልጋል - ቅድሚያ ለራስ!!

ሁለተኛው የችግሩ መንስኤ በሌሎች የተጻፉትን ከኛ ሁኔታ ጋር አስማምተን ስላላቀረብነው ነው፡፡ ከላይ እንደገለጽኩት የራስን አውቆ ሲያበቁ የሌሎችን ማወቁ አስፈላጊ ነው፡፡ ሆኖም ግን የሌሎቹን ስናውቅ እንደወረደ ሲቀርብ ለተማሪዎቹ ግራ አጋቢ፣ የሀገራችንን አውድ ያላማከለ ስለሚሆን መልካም አይደለም፡፡ እንዲያውም አንዳንዴ ተማሪዎች የትምህርት አይነቱን እንዲጠሉት እስከማድረግ ሊደርስ ይችላል፡፡ ስለሆነም ለተማሪዎቹ በመማሪያ መጻሕፍትነትም (text book) ይሁን በማጣቀሻነት የሚሰጣቸው መረጃ በተቻለ መጠን ወደ እኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ ተቃኝቶ መሰጠት አለበት፡፡ አለበለዚያ በሀገራችን ቋንቋ ለሚሰጥ ትምህርት ሳይቀር ተማሪዎች በእንግሊዝኛ የሌሎችን እሳቤ እንደወረደ በማጣቀሻነት እንዲያነቡ ከተደረገ፤ በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሚሰጡ የትምህርት መስኮች ውስጥ አገር በቀል መረጃዎች ሳይጨመሩባቸው ከቀረቡ እና ተማሪዎቹ አገር በቀል መረጃዎችንና ዕውቀቶችን እንዲያነቡና እንዲያገናዝቡ ካልተበረታቱ የሃገራችን ትምህርት የታሰበውን እድገት ለማሳካት ይሳነዋል፡፡ ስለሆነም በሌላው አለም ያሉትን ጠቃሚ ጽንሰ ሃሳቦች በራሳችንም ይሁን በሌላው ቋንቋ ሲቀርቡ የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘቡ መሆናቸው መረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ እውነታው

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# እንግዳችን

## ዩኒቨርሲቲው የያዘውን ራዕይ ከግብ ለማድረስ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የምንገኝ ሰራተኞች የግላችን ራዕይ ማድረግ እንዳለብን ይሰማኛል፡፡

አቶ ቃለዳዊት እስመለዓለም

**የዚህ ወር እንግዳችን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ተቋም የኮምፒዩተር ሳይንስ መምህር ናቸው፡፡ የህይወትና የስራ ተሞክሯቸውን አስመልክቶ ከናይል ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ ቃለ መጠይቁን እነሆ፡፡ መልካም ንባብ!**

ናይል፡- በመጀመሪያ ራስህን ብታስተዋውቀን? የትውልድ ቦታህ፣ አስተዳደግህንና የትምህርት ሕይወትህን ብትገልፅልን?

ቃለዳዊት፡- ቃለዳዊት እስመለዓለም እባላለሁ፡፡ እስከ ስምንተኛ ክፍል ቤተሰቦቼ በሚገኙበት ዱርቤቴ ከተማ ነው የተማርኩት፡፡ እንደ ማንኛውም የማህበረሰቡ ልጆች በትምህርት እና ባለኝ ትርፍ ጊዜ በቤት ውስጥ በተሰጠኝ የስራ ድርሻ መሰረት እያገዝሁ አድጌያለሁ፡፡ ከአንደኛ ክፍል እስከ ስምንተኛ ክፍል በአብችከሊ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እና በአያሌው መኮንን በድርቤቴ ከተማ ተከታትያለሁ፡፡ የሀይስኩል ትምህርቴን ማለትም ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ በዳንግላ ት/ቤት ከዛም የከፍተኛ ትምህርቴን በብሉ ናይል ኮሌጅ እና በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም በኮርያና ጀርመን የተለያዩ ትምህርቶችን ተምሬአለሁ፡፡

ናይል፡- ስለትዳር ህይወትህና ልጆችስ ትንሽ አጫውተን፡፡ ለስኬትህ የባለቤትህን አስተዋፅኦ እንዴት ትገልዋለህ? የአንተን ፈለግ የሚከተልስ ልጅ አለህ?

ቃለዳዊት፡- በጣም የምወዳት እና ለስራዬ ስኬት የቅርብ አማካሪዬና አጋዥ የሆነች ሚስት አለችኝ፡፡ የሁለት ወንዶች ልጆች አባትም ነኝ፡፡ ልጆቼ ገና ህፃን በመሆናቸው ብዙም የሚያውቁት ነገር የላቸውም፡፡ ግን የግል የኤሌክትሮኒክስ ወርክሾፕ ስላለኝ እኔ ስሰራ አብረውኝ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ስለሚያቀብሉኝ እና ስለሚነካኩ በቀላሉ የቴክኖሎጂ ሰዎች ይሆናሉ ብዬ እገምታለሁ፡፡ የትዳር አጋሬ የተማሪ ቤት ጓደኛዬ በመሆንዋና ስራዬን እና ህልሜን ስለምታውቅ ለእኔ ያልታዩኝን ስታሳየኝ፣ ችግሮችን እንዴት በብልሀት ማለፍ እንደምችል ስንወያይ በአጠቃላይ ለእኔ ባለቤቴ ዘውዴ ናት፡፡

ናይል፡- አንተን የጋዜጣችን እንግዳ ለማድረግ ስንነሳ አንዳንድ አንተን በቅርብ የሚያውቁ አብሮ አደጎችህ የፈጠራ ሥራ ፍላጐትህ ከድሮም ጀምሮ ነው ብለውናል፡፡ ይሄ የህይወትህ መሰረት ነውና ብታካፍለን?

ቃለዳዊት፡- በዳንግል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የከፍተኛ ትምህርቴን ስከታተል በነበርኩበት ጊዜ ከመደበኛ የትምህርት ጊዜዬ በተጓዳኝ የራሴን የፈጠራ ስራዎችን በት/ቤቱ ውስጥ በሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ክበብ ስር ብቸኛ አክቲቢስት ነበርኩ፡፡ ስራዎቼንም እየሰራሁ ለት/ቤቱ ማህበረሰብ እና ለተለያዩ እንግዶች አሳይ ነበር፡፡ በተለይ አሁን የምሰራቸው ስራዎች ያኔ ከአገለገሉ እቃዎች በማውጣት የተለያዩ የሙከራ ስራዎችን (prototype) እሰራቸው የነበርኩትን ስራዎች አሁን የኢንጅነሪንግ ጥበብ የሚጠይቀውን ክህሎት በመጠቀም እና የሀይስኩል ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ መድረስ እና መሆን የምፈልገውን የህይወት እቅድ አውጥቼ አሁን የምኖረው ህይወቴ የተጀመረው ከዛሬ አስር ዓመት በፊት የሀይስኩል ተማሪ በነበርኩበት ሰዓት ያወጣሁትን እቅድ ነው፡፡

ናይል፡- የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የወርቅ ሜዳልያ ሸልሞሀል፡፡ ይህን ሽልማት ያገኘሽው ምን አይነት ሥራ በመስራትህ ነው?

ቃለዳዊት፡- የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በሀገሪቱ ውስጥ ችግር ፈች የምርምር እና የፈጠራ ስራዎችን ከአንድ ዓመት ባላነሰ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲያወዳድር ከቆየ በኃላ ስራዬን በአንደኝነት በመምረጥ የወርቅ መዳሊያና ዋንጫ እንዲሁም ማበረታቻ የገንዘብ ሽልማት ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር ኃይለማርያም ደሳለኝ እጅ ሽልማት ያገኘሁበት ስራ በፀሐይ እና በኤሌክትሪክ ሀይል የሚሰራ ዲጅታል የትራፊክ መብራትና መቆጣጠሪያ ግኝት ነው፡፡ ይህ ፈጠራ በመኪና መንገዶች፣ በእግረኛ ቦታዎች፣ በባቡር ጣቢያ፣ በኤርፖርት ጣቢያዎች እንዲሁም በተለያዩ መንገዶች ላይ የተሽከርካሪን እና የእግረኛን እንቅስቃሴ የሚያቀላጥፍ መሳሪያ ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዩጵያ ለተያያዘችው የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ግንባታ ይህ ቴክኖሎጂ በመትከል የትራፊክ አደጋን የሚቀንስ፣ መንገዶች



የትራፊክ መጨናነቅ ገጥሞአቸው ቶሎ እንዳያረጁ የሚቆጣጠር፣ የአሽከርካሪውን ጊዜ የሚቆጥብ፣ እግረኞች በሰለጠነ መልኩ መንገዶችን እንዲያቋርጡና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የሚያስችል የፈጠራ ግኝት ነው፡፡ ቴክኖሎጂው ኢትዮጵያ ለተያያዘችው የኢንዱስትሪ ለውጥ ዋና መሳሪያ ሲሆን ዋና መቆጣጠሪያውም ኢንዱስትሪን አውቶሜት ለማድረግ የሚያስችል በእኔ ዲዛይን የተደረገና የተገጣጠመ ሲንግል ቦርድ ኮምፒዩተር ነው፡፡

ናይል፡- ይህን ፈጠራ ለመስራት ያነሳሳህ ምንድን ነው?

ቃለዳዊት፡- በኢትዮጵያ ደረጃቸውን በጠበቁ መንገዶች ላይ የሚታየው የትራፊክ መጨናነቅ፣ በንብረትና በሰው ሕይዎት የከፋ አደጋ መኖር፣ ከውጭ የሚመጣው የትራፊክ ሲስተም ውድና በብልሽት ጊዜ የመለዋወጫና የባለሙያ እጥረት መኖር እንዲሁም የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ዋና መቆጣጠሪያ በውድ ዋጋ ከውጭ ስለሚመጣ እና ብልሽት ሲገጥመው ፋብሪካው ስራውን ለቀናት ስለሚያቆም ለዚህ ፈጠራ ስራ መነሻ ሀሳቦች ናቸው፡፡

ናይል፡- የፈጠራ ሥራው ውጤት ምንድን ነው?

ቃለዳዊት፡- የፈጠራ ሥራው ውጤት ብዙ ሲሆን ዋነኞቹ

- በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረቡ/ የውጭ ምንዛሬን የሚያስቀር መሆኑ፣
- እጅግ ዝቅተኛ በሆነ የኤሌክትሪክ እና የፀሐይ ኃይል የሚሰራ መሆኑ፣
- ዋናው መቆጣጠሪያና መብራቶች በገመድና ገመድ አልባ ግንኙነቶች መስራታቸው፣
- በቀላሉ የመብራቶችን የቆይታ ጊዜ ማስረዘም እና ማሳጠር መቻሉ፣
- ቴክኖሎጂው የአካባቢ ብክለት የማያስከትል መሆኑ፣
- የከተማን ውበት የሚጠብቅ መሆኑ፣
- የመስማት እና የማየት እክል ላለባቸው እግረኞች መፍትሄ ያለው መሆኑ፣
- የስራ ዕድል የሚፈጥር ቴክኖሎጂ መሆኑና ለብዙ

⇨

# እንግዳችን ...

ሴክተሮች በተለይም አንድን ማሽን አውቶሜት ለማድረግ የሚያግዝ ቴክኖሎጂ መሆኑ፣

ናይል፡- በቅርቡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢንተርፕርነር ማበልፀጊያ ማዕከል ከእስራኤል Technology Transfer group ጋር በመተባበር ከቀረበው የፈጠራ ሥራ ውድድር ላይም ተሳትፈህ አንደኛ ወጥተሀል፡፡ በምን ፕሮጀክት ላይ ነው የተሳተፍከው?

ቃለዳዊት፡- በዚህ ውድድር የተመረጠው ስራዬ በፀሐይ ሀይል የሚሰሩ መብራቶች፣ ሞባይል ቻርጅ ማድረጊያዎች፣ የጫጩት ማስፈልፈያ ኢንኩቤተር እንዲሁም በፀሐይ ሀይል የሚሰራ የመስኖ ውሃ ማጠጫ እና በፀሐይ ሀይል የሚሰራ ጀነሬተር ነው፡፡

ናይል፡- ከውድድሩ ምን ተሞክሮ አገኘህ? ሽልማቱስ ምን ነበር?

ቃለዳዊት፡- ስራዬን ወደ አዋጭ የቢዝነስ ካምፓኒ እንዴት መቀየር እንዳለብኝ እንዲሁም የቴክኖሎጅ ውጤቶችንም ከትንሹ ስራ ጀምሮ ወደገበያ በማቅረብ እንዴት ወደገንዘብ መቀየር እና ማህበረሰቡን ማገልገል እንዳለብኝ ተሞክሮ አግኝቻለሁ፡፡ በሽልማቱ ዕለት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እና የእስራኤል አምባሳደር ከዩኒቨርሲቲው የኢንተርፕርነር ማበልፀጊያ ማዕከል ጋር በመሆን እንዲሁም ከሃያ በላይ የሚሆኑ የእስራኤል Technology Transfer group ስራውን በሰፊው ወደገበያ የሚገባበትን ቅድመ ሁኔታዎችን እናመቻቻለን በሚል ቃል ገብተዋል፡፡

ናይል፡- ይህ ፕሮጀክት ለሀገራችን ምን ጠቀሜታ ይኖረዋል?

ቃለዳዊት፡- በአሁኑ ስዓት የኤሌክትሪክ ስርጭት በተለይ በገጠሩ ማህበረሰብ ዘንድ ስለሌለ እና በእያንዳንዱ አካባቢ የፀሐይ ሀይል እንደልብ ስለሚገኝ ዝቅተኛ ማህበረሰብን ኪስ ያማከለ የቴክኖሎጂ ውጤት በመሆኑ በትንሽ ጎጆ ቤት የሚኖሩ ቤተሰቦች በቂ ብርሃን ከማግኘት ጀምሮ በኤሌክትሪክ ምግብ እስከማዘጋጀት እንዲሁም በእርሻ ማሳቸው ላይ በፀሐይ ሀይል የሚሰራ መስኖ ማጠጫ እና በአካባቢ ላይ ምንም አይነት የካርበን ልቀት ስለሌለው እና የደንን መጨፍጨፍ የሚቀንስ ቴክኖሎጂ ከመሆኑም በተጨማሪ ሀገር ውስጥ መሰራቱ የውጭ ምንዛሬን ያስቀራል ወይም ይቀንሳል፡፡

ናይል፡- ይህ ችግር ፈቺ የሆነ የፈጠራ ሥራ በምን ያህል ገንዘብ ከግለሰብ እጅ ይደርሳል?

ቃለዳዊት፡- ዋናው አላማዬ እርካሽ በሆነ ዋጋ ለገበያ ማቅረብ ሲሆን በፀሐይ ሃይል የሚሰራ ከቤት ውስጥ መብራት ጀምሮ እስከ መስኖ ማጠጫ የሚያገለግለው ቴክኖሎጂ ሀገር ውስጥ በመሰራቱ ከውጪ ከሚመጣው ከስልሳ ፐርሰንት (60%) በላይ ዋጋው ይቀንሳል፡፡

ናይል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 ዓ.ም ከአፍሪካ አስር ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን ተግቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ ለዚህ ራዕይ ስኬት ያንተ አስተዋፅኦ ምን ይመስላል? የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብስ ምን ትመክራለህ?

ቃለዳዊት፡- እንደ እኔ አመለካከት ዩኒቨርሲቲው የያዘውን ራዕይ ከግብ ለማድረስ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የምንገኝ ሰራተኞች የግላችን ራዕይ ማድረግ እንዳለብን ይሰማኛል፡፡ ለዚህም ነው ከመማር ማስተማሩ ጎን ለጎን የማህበረሰቡን ችግር በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፍታት እና የአንድ ምርምር ውጤት ደግሞ ወደ ስራ ተቀይሮ መሬት መውረድ እንዳለበት አምናለሁ፡፡ ስለዚህም ለዩኒቨርሲቲው ራዕይ መሳካት አንድ አስተዋፆኦ ማድረግ ስለምችል እና ማድረግም ስላለብኝ ቴክኖሎጂን በተግባር እያሳየሁ የምገኘው፡፡ ለሌሎች የማስተላልፈው ዩኒቨርሲቲው ግልፅ የሆነ እና የማያሻማ የስራ ድርሻ አለው - መማር ማስተማር፣ መመራመር እና ለማህበረሰቡ የተለያየ አገልግሎት መስጠት፡፡ ስለዚህ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚገኘው ተማሪ፣ መምህር እንዲሁም የአስተዳደር ሰራተኛ የተሰጠውን የስራ ድርሻ የእኔ ስራ ብሎ በእየለቱ በደንብ ከተወጣ ዩኒቨርሲቲው አይደለም ከአፍሪካ በአለም ምርጥ መሆን ይችላል፡፡ ዋናው ነገር ዓላማን ነድፎ ለእያንዳንዱ ሰከንድ እና ደቂቃ ክብር በመስጠት መትጋት ስለተቻለ ነው ማርስ እና ጨረቃ በሰው የቴክኖሎጂ ውጤት የተደፈሩት፡፡

ናይል፡- ለዩኒቨርሲቲው ይህ ይጠቅመዋል የምትለው አስተያየት ካለህ?

ቃለዳዊት፡- ዩኒቨርሲቲው አንጋፋ በመሆኑ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተሰሩ በጣም ብዙ ስራዎች እና ብዙ እውቀቱና ክህሎቱ ያላቸው ሰዎችም ቢኖሩም የማስተዋወቁ ስራ ብዙም የተሰራ አይመስለኝም፡፡ ዩኒቨርሲቲ የአዲስ ሀሳቦች እና ቴክኖሎጂዎች መፍለቂያ እንደመሆኑ መጠን የተሰሩ እና የተሞከሩ ስራዎችን





ማሳያ የሆነ ቴክኖሎጂ ጋለሪ (ሙዚየም) ስለሌለ ማን ምን ሰራ? መቼ ሰራ? የሚሉ መረጃዎችን ማግኘት ከባድ ይሆናል፡፡ ለዚህም የማስተላልፈው መልዕክት የአዲስ ስራዎችን ማስቀመጫና የስራ ውጤቶች ማሳያ የሚሆኑ ማእከሎች ቢኖሩ ጥሩ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ቴክኖሎጂ ከሚጻፍ የሚታይ ሲሆን ልብ ይገዛል በአዕምሮም ይመዘገባል፡፡

ናይል፡- ለሌሎች የምታስተላልፈው መልዕክት ካለህ?

ቃለዳዊት፡- ለሌሎች የማስተላልፈው መልዕክት ከዩኒቨርሲቲ ጋር ተቀራርቦ መስራት በጣም መለመድ ያለበት እና የሌሎች ያደጉ ሀገሮች ተሞክሮ ሲታይ ዩኒቨርሲቲ እና ኢንዱስትሪው በጣም የተቆራኘ የስራ ግንኙነት አላቸው፡፡ ስለሆነም ሁሌም የውጭ ቴክኖሎጂ በመጠቀም መቀጠል ጥገኝነትን ስለሚያስከትል ኑ ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የማይፈታ ቴክኖሎጂ የለም እና አብረን እንስራ እላለሁ፡፡

ናይል፡- በመጨረሻ ማመስገን የምትፈልገው አካል ካለህ እድሉን ልስጥህ?

ቃለዳዊት፡- በመጀመሪያ ብርታት እና ለተስፋዬ ስንቅ ለሆነችው ድንግል ከእነልጇ ክብር ምስጋና ይድረስ፡፡ በመቀጠል በመልካም ስነ ምግባር እና በጥሩ የስራ ባህል ላሳደጉኝ አባቴና እናቴ እንዲሁም ወንድሞቼና እና እህቴ፣ ከጎኔ ለማትለየው እና ለምታበረታታኝ ባለቤቴ በመቀጠልም ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች እና ጓደኞቼ እንዲሁም ለስራዬ መሳካት ላገዙኝ ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ ስል የስራዬም ውጤት በእጃችሁ እንዲደርስ ተግቼ እሰራለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡ እናንተንም እግዚአብሄር ያክብርልኝ፡፡

ናይል፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን!

# ሸኝና ተሸኝ

በደስታ ተከስተ
ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀጥታ አገልግሎት

አንድ ያልታወቀ ተናጋሪ ወሬ ሲቦተልክ እንደሰማሁት ከሆነ ‹‹ሀበሻ ከእድሜው 1/3ኛው ጊዜ የሚያባክነው ሰላምታ ሲለዋወጥ ነው›› ብሎ ነበር፡፡ ነገሩ እውነት ይሁን ቧልት ወደፊት እንደ አስፈላጊነቱ ጥናት እንዲደረግበት ለተመራማሪዎች በመተው እኔ ግን ጊዜና ፊደል ለመቆጠብ ስል እንደ ፌስ ቡክ ላይ ቻት ሃይ ብያችኋለሁ ‹‹ሀይ›› ማለት ምን ማለት ነው? የሚለኝ አንባቢ ካለ ምን አልባት በፌስ ቡክ ከእኛ እናንተ የናይል ጋዜጣ አዘጋጆችና አንባቢያን ሆይ እወዳችኋለሁ አከብራችኋለሁ እንደምን ሰነበታችሁልኝ... ለማለት ይሆናል፡፡

ወገኖቼ ትርጉሙን ብሳሳት አትፍረዱብኝ ምክንያቱም የእንግሊዘኛና የመረጃ እጥረት አለብኝ፡፡ ምክንያቴ ደግሞ ትምህርቴን እየተማርኩኝ ያለሁት ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ አሁነኛ ድረስ የኑሮ ሁኔታ ሆኖብኝ በማታ ክፍለ ጊዜ ነው... ተው እንጂ የኛ ፀሐፊ! የማታ ተማሪ እንግሊዘኛ አያርፍም ያለህ ማን ነው? በማለት ልታስተካክሉኝ ያሰባችሁ አንባቢዎቼ ካላችሁ እኔ እንደዛ ለማለት ፈልጌ አይደለም፡፡ የግል ገጠመኜን ላወጋችሁ በማሰብ ነውና እለፉኝ፡፡

በእኛ ትምህርት ቤት ብዙን ጊዜ በእንግሊዘኛ ክፍለ ጊዜ መብራት ይጠፋል በዚህ ምክንያት የተቆራረጠ የእንግሊዘኛ እውቀት ነው ያለኝ፡፡ ለምሳሌ መምህራችን ገና ወደ ክፍል እንደገቡ “Good evening Students” እንዳሉን እኛም በአንድ ድምፅ “Good evening teacher” እንዳልን መብራት ድርግም ብሎ ይጠፋል፡፡ ከዚያም እኛ እንደቆምን መምህሩ ተመልሰው ይወጣሉ፡፡ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ መምህሩ ቀጥሎ ሊናገሩ የነበረውን የእንግሊዘኛ ቃል ሳንሰማው እንቀራለን፡፡ እንግዲህ ለዚህ ነው የተሟላ እንግሊዘኛ ቋንቋ ሳናውቅ ትምህርታችንን የምንገፋው፡፡

እርግጥ ነው ትምህርት ብቻ ሳይሆን ስራዬንም የምሠራው ማታ ማታ ነው፡፡ እንዲያውም “ተረኛ ነኝና እንዳትሸበሪ... ስለይሽ አዝናለሁ አልማዝ ደህና እደሪ” የሚሉት የድሮ ዘፈን ዛሬ ላይ ሆኜ በራዲዮ ስሰማው ለእኔ የተዘፈነልኝ እየመሰለኝ ሆዴን ባር ባር ይለኝል፡፡ “አይ ህይወት እንደዚህ ናት” አለች አሉ ቢዮንሴ፡፡ ፈጣሪ አምላክ ቀኑን ለሠራዊት ሌቱን ለአራዊት መድቦ ቢከፍለውም በእኔ ህይወት ግን የተገላቢጦሽ ሆኖብኛል፡፡ ይሁን ብቻ “ያልፋል ግን እስኪያልፍ ያለፋል” ይላሉ አበሾች፡፡

የእኔን ሁኔታ በቅርበት የሚያውቀው አንድ የመንደራችን ተረበኛ ወጣት ከእለታት በአንዱ ቀን በምሽት ወደ ሥራ ቦታዬ ስሄድ አግኝቶኝ “ጋሽ እምሩ እኔ ያልገባኝ የአንተ ጉዳይ ነው” ሲለኝ መቼም ለነገር መሆኑ ቢገባኝም “ምኔ ነው ያልገባህ?” ስለው አብረውት ያሉትን ጓደኞቹን ግራና ቀኝ ተመልክቶ “ቆይ እስቲ እኔ ከማውቅህ ጀምሮ ትምህርት የምትማረው በማታ ነው፣ ሥራም የምትሠራው በማታ ነው፤ ለመሆኑ የዘር ሀረግህ ከሌሊት ወፍ ይሆን እንዴ?” ሲለኝ እርሱን ጓደኞቹ በሳቅ አጅበው ሲያሞቁት እኔ ግን አባባሉ በንዴት አብከነከነኝ፡፡ ቆይ ደሃ ነኝ እንጂ መቀለጃ ነኝ እንዴ ብዬ ልናገር ስል “ለማንኛውም የድኤንኤ ምርመራ ማድረግ ይኖርብሃል” ብሎኝ እየገለፈጠ እንደቆምኩ ጥሎኝ ሄደ፡፡

ውድ አንባቢዎቼ በዚህ ጎረምሳ ወጠጤ ልቡ ያበጠበት አነጋገር ውስጤ በብዙ ሃሳብ ተሞላ፡፡ ንዴት ጨጓራዬን ሲያቃጥለኝ ለማንኛውም... አልኩና ለእራት መብያ ከያዝኳት የውሃ ኮዳ ላይ ሁለት ጊዜ ፉት ካልኩኝ በኋላ ትንሽ ቀዝቀዝ ሲያደርገኝ ውሃን ለሰው ልጆችና ለፍጥረታቱ የፈጣሪ አምላክ መድሃኒያለምን ተመስገን አልኩት፡፡

> ምድረ ሀበሻ ለሊቱ
> አልበቃ ብሎት ቀን ሲተኛ
> በሚውልበት ሀገር አንተ ደግሞ
> የምሽት ሥራ እየሠራህ መተዳደርህ
> ያስመሰግንሃል፡፡ ምናለ ከፊል አርሶ
> አደር ሆነህ ቢሆን ኖሮ! ለሽልማት
> ቀርበህ የጠቅላይ ሚኒስቴሩን እጅ
> ትጨብጥ ነበር፡፡

ውሃ ባልይዝ ኖሮ ምን ይውጠኝ ነበር፡፡ አልኩና ደጋግሜ ተጎነጨሁለት፡፡ ምን አልባት የሰው ልጅ አመጣጡ እንደዬ ፍልስፍናው ይለያያልና በማለት ስለ ማንነቴ ለማወቅ በሃሳቤ በመራመርም የተወለድኩበት ዕለት ጊዜው ወደ ማታ ከመሆኑ ውጭ ያገኘሁት ነገር አልነበረም፡፡ ወደ መስሪያ ቤቴ አቅራቢያ ልደርስ ትንሽ ሲቀረኝ የመንደራችን እድር ሰብሳቢ የሆኑትን አቶ ቁምላቸው ጋር ድንገት ተገናኘን፡፡ እርሳቸውም ለሰላምታ የዘረጋሁላቸውን ቀኝ እጄን በኃይል እያወዛወዙ “እምሩ አንተ የመንደራችን አንበሳ ነህ እንዲያ ነው በርታ፣ ጎሽ አንተ ‘ኮ ለቀበሌው ነዋሪ አርዕያ የምትሆን ሰው ነህ፣ ምድረ ሀበሻ ለሊቱ አልበቃ ብሎት ቀን ሲተኛ በሚውልበት ሀገር አንተ ደግሞ የምሽት ሥራ እየሠራህ መተዳደርህ ያስመሰግንሃል፡፡ ምናለ ከፊል አርሶ አደር ሆነህ ቢሆን ኖሮ! ለሽልማት ቀርበህ የጠቅላይ ሚኒስቴሩን እጅ ትጨብጥ ነበር፡፡” ሲሉኝ በወጣቱ አነጋገር ቀዝቅዞ የነበረው ሞራሌን አነቃቁት፡፡ “ዝር ይውጣልዎት” በማለት መረቅኋቸው፡፡ አያይዤም ከአያቴ የሰማሁትን ጋሼ ቁምላቸው “የማታ እንጀራ ይስጥዎት” ስላቸው “አይ እምሩ እኔ ዘበኝነት አልፈልግም” ሲሉኝ ሽርደዳ ይሁን ሽንገላ ነገሩ ሳይገባኝ ተለያየን፡፡

በእርግጥ ሥራዬን የምሠራው ወድጄና ፈቅጄ ከዘመድ አዝማድ ተማክሬ ነው፡፡ ትምህርት የምማረው ግን ለሁለት ጉዳዮች ስል ነው፡፡ የመጀመሪያው ተምሬ በጥሩ ውጤት በመመረቅ ከልጅነቴ ጀምሮ ስመኘው የነበረው የውሃ ተመራማሪ ታላቅ ምሁር ለመባልና በሞያዬ ሀገሬንና ወገኔን መጥቀም በማሰብ ነው፡፡ የውሃ ነገር አይሆንልኝም ሰውና ውሃ የማይስማሙት ወንዝ ሲሞላ ብቻ ነው፡፡ ሀገራችን ካሏት ሀብቶች መካከል ከሰው ቀጥሎ ውሃ ነው፡፡ እንዲያውም የሶስተኛ ክፍል የሳይንስ አስተማሪያችን ሲናገር እንደሰማሁት ከሆነ ከሰውነታችን 60% በውሃ የተገነባ ነው፡፡ ቀሪው 40% ግን አፈር መሆኑ ነው፡፡ መጽሐፉ ቅዱስ እንደሚለው ‹‹ሰውን ከአፈር አበጀው›› እንግዲህ ከዚህ ቀን ጀምሮ ነው የውሃ ተመራማሪ ለመሆን የወሰንኩት፡፡

የመማሬ ሁለተኛ ምክንያት ደግሞ ለ‹ሁአዬ› ስል ነው፡፡ ለመሆኑ ‹‹ሁአዬ›› ማንናት? ብትሉኝ አብራኝ የምትማር የክፍል ጓደኛዬ ናት፡፡ ስሟ ‹‹ሁሉሀገርሽ›› ነው፡፡ እኔ ግን በጣም ስለምወዳትና ስለማፈቅራት ለማቆላመጥ ስል ‹‹ሁአዬ›› እያልኩ እጠራታለሁ፡፡ መቼም እናንተዬ የፍቅር ነገር ሆኖብኝ ስሟን ለማቆላመጥ ያልፈለኩት ቃላት ያልገጣጠምኩ ፊደል አልነበረም፡፡ ከመደበኛ ስሟ ጋር የሚገጣጠም ሆኖ ያገኘሁት ይህን ነው፡፡ በመሆኑ በዚሁ መጥራት ጀምሪያለሁ፡፡ ‹‹ሁአዬ››ም ተስማምቷታል፡፡ እስካሁን በእርሷ በኩል ያለውን የልቧን ሃሳብ ባልረዳውም እኔ ግን ውስጥ እግሬ እስኪቃጠል ድረስ አፈቅራታለሁ፡፡ መቼም አንዳአንዶቻችሁ ‹‹የውስጥ እግርን የሚያቃትል ፍቅር ሳይሆን ፈንገስ ነውና በውሃ ታጠበው›› እንደምትሉኝ ይገባኛል፡፡ ‹‹ያልተያዘ ግልግል ያውቃል›› ነውና ነገራችሁ ግድየለም ያሻትሁትን ብትሉኝም በሽታዬን የማውቀው እኔ ነኝ፡፡

የሁአዬ ፍቅር የጀመረኝ በመሸኘት ነው፡፡ ከትምህርት ቤት ስንለቀቅ ስለሚመሽና ሰፈሯ እሩቅ በመሆኑ ‹‹ሸኝኝ›› ትለኛለች፡፡ በመጀመሪው ቀን እንዴት እምቢ እላታላሁ በማለት መሸኘት ጀመርኩ፡፡ እየቆየ ስሄድና እየተግባባን ስንመጣ ግን እኔው እራሴ ‹‹ሁአዬ ልሸኝሽ›› ማለት ጀመርኩ፡፡ እንዴት በፍቅሯ እንዳጠመደችኝ አልገባኝም ወይም እንዴት ላፈቅራት እንዳልቻልኩ ግር ይለኛል፡፡ እኔና እርሷ ስንተያይ የእድሜ ልዩነታችን ይሰፋል፡፡ ከእለታት በአንዱ እለት እየሸኘኋት በአጋጣሚ የሚያውቃት ልጅ ያገኛታል፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ‹‹ተዋወቀው›› ስትለው እጁን እየዘረጋልኝ “ይቅርታ አባትሽ ናቸው?” ሲላት በንዴት የዘረጋልኝን እጁን ጠምዝዤ ልሰብረው አስቤ ነበር፡፡

ያም ሆነ ይህ እኔና እሷ ተግብተናል፡፡ እኔ እሸኛታለሁ እርሷም ትሸኝልኛለች፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሁአዬን አግብቼ ብኖርስ ስል አሰብኩ፡፡ ይህንኑ ሃሳቤን በፍቅር ላቀርብላት ወሰንኩ ለማንኛውም ካልተበከለ በቀር ውሃና ምክር ለሰው ጠቃሚ ነው አልኩና ማፍቀሬን ለሚያውቅ ባልንጀራዬ ሳማክረው “ኸረ ተው እምሩ ልጅቷ እንደሰማሁት ከሆነ ለትዳር አትሆንህም እርሷ መንገደኛ ነች፣ ከብዙ ጎረምሶች ጋር ትታያለች” አሉ፡፡ ቢለኝ የምቀኛ ወሬ ነው ሁአዬ ይህን አታደርግም! አንገቴን ለከራቫት እሰጣለሁ አልኩና ነገሩን አጣጣልኩበት፡፡ እናም በጉዳዩ ገፍቼበት በአንድ እለት ምሽት እየሸኘኋት ሳለ ልነግራት ወሰንኩ፡፡ በእለቱም አብረን እየተራመድን ከአሁን አሁን ልንገራት አልንገራት እያልኩ ሳመነታ ዘወትር ሸኝቻት የምንለያይበት ስፍራ ስንደርስ “በል ተመለስ አመሰግናለሁ ቻው” ብላኝ ከአጠገቤ ተፈተለከች፡፡ በቆምኩበት በራሴው ሁኔታ ተበሳጨሁ፡፡ ደካማ፣ ፈሪ ነኝ ማለት ነው? እንዴት እፈራለሁ ያኔ ባድመ ላይ ስዋጋ እንዴት አልፈራሁም? በእርግጥ “ጦር ሜዳ ገብቶ ከሚፈራ ወታደር ይልቅ ሴትን ለፍቅር መጠየቅ የሚፈራው ይበልጣል›› ይል ነበር አሉ ጀግናው አብዲሣጋ፡፡

እራሴን በራሴ አጀግኜ ቶሎ ተከትያት በመሄድ እቤቷ ሳትደርስ ልነግራት አሳብኩና የጥድፊያ እርምጃዬን ቀጠልኩ፡፡ ዘዋራውን መንገድ አልፌ ትንሽ እንደተራመድኩ ከፊት ለፊቴ ‹ሁአዬ ከአንድ ወጣት ጋር ቆማ ስታወራ ሳያት ‹ወይኔ ውኃው በላኝ› አልኩ በድንጋጤ፤ ልቤ በደረቴ ሾልካ ልትወጣ ስትታገል አይኖቼ ባለማመን አፍጥው ያያሉ፡፡ መንፈሴ በንዴትና በቅናት መጋል ጀምሯል፡፡ እንደምንም እራሴን በመግዛት “እስቲ ልታገስና መጨረሻቸውን ልመልከት መታገስ ጥሩ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ብዙ አመታትን ታግሳ ነው፤ አባይን ወንዝ መገደብ የጀመረችው” በማለት እነርሱ ሳያዩኝ እያየኋቸው የሚሉትን ለመስማትና የሚያደርጉትን ለማረጋገጥ በስልት እንደሚራመድ ወታደር እያደባሁ ተጠጋኋቻው፡፡ አንገቷ ላይ ተጠምጥሞ ከንፈሯን አንድ ጊዜ ከጎረሳት በኋላ “የእኔ ቆንጆ እስከዚህ ድረስ ብቻሽን በጨለማ ስትመጭ አትፈሪም እንዴ?” ሲላት “ኸረ ብቻዬን አልመጣም እኮ የሚሸኘኝ ሰው አለ” ስትለው እንደ መኮሳተር ብሎ “ማነው እሱ ደግሞ አንችን የሚሸኝሽ?” አላት፡፡ “አንተ አታውቀውም የክላሳችን ትልቁ ሰውዬ ነው፡፡ ስለሚሸኘኝ እንጂ ከእሱ ጋር መሄድ አልፈልግም ነበር፡፡” ስትለው ከዚህ በኋላ በዚያ ስፍራ ቆሜ ማየትም መስማትም አልቻልኩም፡፡ ትዝ የሚለኝ በዚያ ምሽት ልክ እንደ አበደ ሰው ድምፄን ከፍ አድርጌ “የግሌ ነሽ ብዬ እንድኮራብሽ መንገደኛው ስብር ይበል እግርሽ” እያልኩ ወደ ምሽት ሥራዬ መሄዴን ነው፡፡

# የግጥም ጥግ

## “የፍየል ወገኖች”

ተመራማሪ ነኝ
ለብዙ ዘመናት በደን ሀብት ላይ ጥናት ያደረግሁኝ
ዛሬም እንደድሮው ጥናቴን ቀጠልሁኝ
በተቀጠረው ቀን እንደሚከተለው ለህዝብ አስደመጥሁኝ
የአገራችን ጫ ካ 43% ድሮ እንዳልነበረ
ዛሬ በእኛ ዘመን 3% ደረሰ ሁሉም አከተመ
የደን መራቆት እጅግ አሳሰበኝ
የሀገር እርቃን መሆን እንቅልፍ እኔን ነሳኝ
ይህ የደን መራቆት በዚህ ከቀጠለ ለቀጣይ አመታት
እንኳንስ በቁጥር ሚገለፅ በፐርሰንት
የሚታይ ይጠፋል የዛፍ ዘር የእንጨት
ስለዚህ ወገኔ በጣም አስቡበት
    አልሁና ጨ ርሸ
    አየሩን ጠቅሸ
    ጥያቄ ካላችሁ
    በጣም ያልገባችሁ
እጅግ በደስታ ነው ወልከም (WELL COME) ስላችሁ
አልሁና ቁጭ ብየ እጅ ስመለከት
አንድ ሰው አይቼ ቀጥል ወዳጀ አልሁት
    እርሱም ተነሳና
“ክቡር ተመራማሪ እጅግ አሳስቦዎት የመሬት መራቆት
ይህን በማቅረብዎ ልገልጸው አልችልም ያለኝን አድናቆት
ግን ይህንን ያህል ለመሬት መራቆት ከተጨነቁለት
ሰው ከልብስ ተራቁቶ እርቃን ቆሞ ሲያዩት
ልክ እንደ ፍየሎች ሀፍረቱን ሳይሸፍን ነውሩን ሁሉ ትቶት
ከእንስሳት ሁል አንሶ ወጥቶ ከሰውነት
ብዙ ጉድ አይተናል የሚያሳፍር በእው ነት
ሰው የእራሱን ገላ መሸፈን ካልቻለ
ስለምድር ያስባል ብሎ የሚል ካለ
እራሱም ሞኝ ነው ማስተዋል ያልቻለ
ስለዚህ እርስዎ ይህን እንዴት አዩት?
ወዴትስ ሊሄድ ነው ኢትዮጵያዊነት?”
    ብሎ ተቀመጠ
ታዳሚውም ሁሉ ፀጥ አለ በአግራሞት
እኔም ግራው ገብቶኝ በጥያቄው ክብደት
የማው ቀው ባይኖርም ዝም ላለማለት
    ጥሩ ጥያቄ ነው አዳምጡ ሁላችሁ
    ባይሆን ታዳሚዎች ከዚህ ውስጥ ያላችሁ
    የፍየል ወገኖች እርቃኖች ካላችሁ
    እናንተው ልበሱ ሌላውን ትታችሁ
    የሰው ልጅ ተነግሮት ካላስተካከለ ምንድን ትላላችሁ?
    ስለዚህ ብትችሉ ባይሆን እናንተ እንኳ ለአለሙ ሁሉ ምሳሌ ሆናችሁ
    ምግባር ልብስ ልበሱ ይወገድ እርቃኑ ደንቆሮነታችሁ።

(በዩኒቨርሲቲ ውስጥ እርቃናቸውን ለሚጓዙ ተመራቂ እህቶች)

መኳንንት ፈንታሁን
በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት
የአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ተመራማሪ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

### ናፍቆቴ

አልፈልግም እኔ ስለ ፖለቲካ
እንኳን በምላሴ በጥፍሬም አልነካ
ግን ደግሞ አልሻም ክፉ ነገር ማየት
ሰው በሰውነቱ መከበር አለበት
ሰላም እንዲነግስ በዚህች ምድር
ውስጤ ይናፍቃል እውነትና ፍቅር

### በፍቅር መበቀል

አንብበን ከሆነ የኢየሱስን ምግባር
ትልቅ ጉዳይ አለ ከእርሱ የምንማር
ይሁዳ በተንኮል አብሮት እየኖረ
ፊቱን አልነሳውም አጎረሰው እንጀራ
    ወጭት እየነከረ።
  ኋላ ግን ……
የመስቀል ላይ ሞቱን ከጇው ተመልክቶ
እራሱን አጠፋ በፀፀት ተሞልቶ።
  ፍቅርን ስናሳየው …….
የበደለን ጠላት ህሊናው ሞግቶት እሩሁን ከቀጣ
በቃ! ከዚህ በላይ በቀል ከየትም አይምጣ።

በደስታ ተከስተ
ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀጥታ አገልግሎት

### ህይወት አንቺ እና እኔ

ህይወት አንችና እኔ ስትቀድሚኝ ስቀድም
ስትገፊኝ ስገተር ስትስቢኝ ስለግም
    ወይ አለመታደል
    እንደ እድል ሆኖብኝ፣
ስትጠሪኝ ሳቅማማ ስትሄጂ ስከተል
ስትቆሚ ስመለስ ስትሮጭ ሳዘግም
    ወይ አለመታደል
    እንደ እድል ሆኖብኝ
እንዳላየሁ ስሆን ፊትሽን ስትዞሪልኝ
አንገትሽን ስትደፊ እኔ ሳፈጥብሽ
    ወይ አለመታደል
    እንደ እድል ሆኖብኝ
አምርረሽ ስትተይኝ አንቅረሽ ስትተፊኝ
ዛሬ ግን ለመንኩሽ በጣም ተማፀንኩሽ
ትንሽ ብታዝኝልኝ ተስፋ እንዳላጣብሽ

በሰለሞን ሙሉ

### ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን

- የተለያዩ ጹህፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# የሃገሩን ሰርዶ...

ከገጽ 7 የዞረ

ግን የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡

ሶስተኛው መንስኤ ደግሞ አካባቢያችን ላሉ እውቀቶች ዋጋ ስላልሰጠን ነው፡፡ በሃገራችን ለብዙ የትምህርት ዘርፎች ግብዓት የሚሆን እውቀት አይጠፋም ነበር፡፡ በሕክምና ሳይንስ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች በሙሉ፣ በሙዚቃ፣ በፍልስፍና፣ በኪነ ጥበብ፣ በስነ ጽሑፍ፣ በስነ ከዋክብት፣ በምህንድስና፣ በባሕል ጥናት፣ በጋዜጠኝነት፣ በሕግ፣ በስነ ልቡና፣ በሌሎችም አገራዊና አካባቢያዊ እውቀት አልጠፋም፡፡ እነዚህ አገር በቀል እውቀቶች ደግሞ ያውም ዓለም እንደዛሬው ገና ባልነቃበት ዘመን በሃገራችን ቋንቋዎች በስፋት ተጽፈዋል፤ ያልተጻፉና የሚጽፋቸውን የሚናፍቁም እንደዚሁ፡፡ ይህንንም ዕምቅ ዕውቀት ወደ ዘመናዊው ትምህርት መግባት ባለበት አግባብ አጥንቶና አጠናቅሮ ማካተት ያስፈልጋል፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ይህንን ስናደርግ ብዙም አይስተዋልም፡፡ እንዲያውም ያገራችንን ፈላስፋዎችና የጥንት ምሁራን ስራዎች በሌላ አገር ሰዎች ሲፈለጉ፣ ሲጠኑና ሲቀርቡ እናስተውላለን፡፡ በማንም ይሁን መጠናታቸው ደስ ይላል፡፡ እራሳችን በበቂ ሁኔታ አለማጥናታችን፣ አለማቅረባችን፣ በትምህርታችንም አለማካተታችን ግን ያማል፡፡ ስለሆነም የራሳችን የሆኑ የታሪክ፣ የማንነት መገለጫዎቻችንን፣ ከትውልድ ትውልድ መልካም እሴቶችን የምናስቀጥልባቸውን ጠቃሚ መረጃዎችን መሰብሰብ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ፡፡ እነዚህን መረጃዎች መሰብሰቡ አንዱ ስራ ነው፡፡ ሌላው ግን ዘመኑን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ተጠንተው፣ ተጽፈው፣ ተተርጉመው፣ ሊነበቡ በሚችሉበት ሁኔታ መቅረብ አለባቸው፡፡

ይህን ማድረግ ደግሞ በመስኩ የተሻለ ቁመና ያለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስራ መሆን ይገባዋል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር እና የመማር ማስተማር ተቋማት እንደመሆናቸው ማጣቀሻ ሊሆኑ የሚችሉ አገር በቀል እውቀቶችን በመለየት እንዳለ የሚወሰዱትን እንዳለ በመውሰድ፣ መተርጎም ያለባቸውን በመተርጎም/በማስተርጎም፣ በተሻለ ቴክኖሎጂ መቅረብ ያለባቸውንም እንደዚሁ በማድረግ ምቹ ሁኔታ ሊፈጥሩ ይገባል፡፡

ከላይ የተነሱት በትምህርት ስርዓታችን ላይ ዘመናዊ ትምህርት በሀገራችን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ተጋርጠው የኖሩ ችግሮች ሲጠቃለሉ “ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ” ካለማረስ የመጡ እንከኖች እንደሆኑ መረዳት አያዳግትም፡፡ የተማረ የሰው ኃይል ለማምረት በሀገራችን የእውቀት ማረሻና በሬ መጥመድና ማረስ አለብን፡፡ አለበለዚያ የራሳችንን እያሳረርን የሰው አማሳዮች መሆናችን ይቀጥላል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ደግሞ የእኛንም የዕውቀት ሃብት ሌሎች ሊረዱት በሚችሉበት ቋንቋና አቀራረብ ማቅረቡም እንዳለ ሆኖ ቅድሚያ ለአገር በቀል የእውቀት ሃብት መስጠትና የሌሎችን እውቀት ስናመጣ ከአገራችን ነባራዊ አውድ ጋር ማዛመዳችን መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲም በአገሪቱ ካሉ አንጋፋ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አንዱ እንደመሆኑ ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎች ከመስራት አንጻር ብዙ ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ አንጻር የጀመራቸው ስራዎች መልካም ናቸው፡፡ በምርምሩ ዘርፍ እጅግ በጣም ጥሩ የሚባል ስራ እየተሰራ ሲሆን በተለይም በቁጥር በርከት ያሉ የምርምር ማዕከላትና ተቋማት መቋቋማቸው ትልቅ መሰረት መጣሉን ያሳያል፡፡ የምርምር መጽሔቶች በየሙያ ዘርፉ እየተጀመሩ ሲታይ መልካም ነው፡፡ የምርምር ስራዎች በየሳምንቱ በየመድረኮቹ እየቀረቡ ውይይት መደረጉ ይጠንክር የሚያስብል ነው፡፡ ለተመራማሪ ምሁራን የማትጊያ ሽልማቶች ሲሰጥ ማየቱ ጥሩ ነው፡፡ ለወደፊቱ ደግሞ እየተሰሩ ያሉት የምርምር ስራዎች ጥራትና የህትመት ሁኔታ አሁን ካለበት እየተሻሻለ እንደሚመጣ ተስፋ አለኝ፡፡ በምርምር የተገኙ ውጤቶች ወደ መማር ማስተማሩ እየተካተቱ ምርምሩና ማስተማሩ እየተመጋገቡ የሚሄዱበትን ድልድይ በጠነከረ ሁኔታ መገንባትም አለበት፡፡

በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ስራ እየሰሩ ካሉ ተቋማት መካከል አንዱ የአማርኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ተቋም መመስረትና ወደ ስራ መግባት ነው፡፡ ይህ ተቋም በሕዳር 2006 ዓ.ም ተመስርቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሃገሪቱ አሉ የሚባሉ ምሁራንን፣ ደራሲያንን፣ ጋዜጠኞችን፣ የቲያትርና የፊልም ባለሙያዎችንና የሃይማኖት ተመራማሪዎችን በመጋበዝ የዚህን ተቋም አላማ በማቅረብ ሃሳቦችን ተቀብሎ ማሻሻያዎችን በማድረግ የአመታት እቅድ አውጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ የቋንቋውን ታሪክ የማጥናት፣ የአጠቃቀም ስርዓቱን የመፈተሽና የማስተካከል፣ በቴክኖሎጂ የማዘመን፣ በሌላ ቋንቋ የተጻፉ ጠቃሚ ስራዎችን የመተርጎምና የማቅረብ፣ በዘርፉ ተግባራዊ የስራ ላይ ስልጠናዎችን ለሚመለከታቸው አካላት የመስጠት ስራዎችን እየሰራም ይገኛል፡፡ አሁን በቅርቡ እንኳን ይህ ተቋም “ፎክሎር ምንነቱና የትምህርቱ የትኩረት አቅጣጫ” በሚል ርዕስ በአቶ ሰሎሞን ተሾመ የተሰናዳውን መጽሐፍ በዩኒቨርስቲው አስመርቋል፡፡ ይህ መጽሐፍ ያገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ ለሚለው ብሂል ትልቅ ጅምርና ማሳያም ነው፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ተቋም ሀ ብሎ የጀመረው ጉዞ አድማሱ የሰፋ ስለሆነና ጉዞውም የማንነት፣ የእውቀትና የእድገት ጉዞ ስለሆነ ሊበረታታ ይገባዋል፡፡ እንደዚህ ተቋም ሁሉ ሌሎች የትምህርት ዘርፎችም በየሙያ መስካቸው ያሉትን ሃገራዊ እውቀቶች በመፈለግ፣ በመመርመር እንዲሁም በአገር አቀፍ ብሎም በአለም አቀፍ ደረጃ ሊነበቡና ሊታወቁ በሚችሉበት መልኩ አሰናድተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመጨረሻም የባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ የተሻለች ኢትዮጵያን ለመፍጠር በምርምሩ የጀመረው ስራ ጅምሩ መልካም መሆኑን አይቶ ከስራው ስፋት አንጻር ግን ምንም እንዳልሰራ ተገንዝቦ በቁርጠኝነት ወደፊት መግፋት እንዳለበት በማሳሰብ ጽሁፌን አበቃለሁ፡፡

ቸር እንሰንብት!

# የባሕር ዳር ከተማን ታሪክ የሚዘክረው “አቦካቦት” የተሰኘ መጽሐፍ ተመረቀ

በአምሳሉ ጥላሁን

የባሕር ዳር ከተማ አመሠራረትና የነዋሪዎችን ታሪክ የሚዘክር ‹አቦካቦት› በሚል ርዕስ የተፃፈው መጽሐፍ የዩኒቨርሲቲያችን ባልደረባ በነበሩት በአቶ ያረጋል ገረመው ታህሳስ 2008 ዓ.ም ከቀኑ በግራንድ ሆቴል በደማቅ ሁኔታ ተመረቀ፡፡ መጽሐፉን የባሕር ዳር ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት ተወካይና የትምህርት መምሪያ ኃላፊ አቶ ሙሉቀን አየሁ እና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ በጋራ መርቀውታል፡፡

በምረቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ እንደተናገሩት የባሕር ዳር ከተማን ታሪክ ከዚህ በፊት በተደራጀ ሁኔታ ጽፎ ያቀረበ እንደሌለና አሁን በአቶ ያረጋል ገረመው የቀረበው የከተማዋን እንዲሁም ነዋሪዎቿን በሚዘክረው ‹አቦካቦት› መጽሐፍ ግን የከተማውን ታሪክ በጥልቀት የሚያትት በመሆኑ ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡ ይህ መጽሐፍ ለወደፊት ለታሪክ ተመራማሪዎች በማጣቀሻነት የሚያግዝ እንደሆነ እና የባሕር ዳር ከተማንና የነዋሪዎችን ታሪክ ለትውልድ የማስተላለፊያ መንገድ መሆኑን ዶ/ር ፍቅረሰላም ጠቁመው ለወደፊት በዚህ ስራ እንደማያቆሙና ከዚህ በበለጠ የባሕር ዳር ከተማን እና የነዋሪዎችን ታሪክ በሌላ መጽሐፍ ይዘው እንደሚመጡ ያላቸውን እምነት አስተላልፈዋል፡፡

አቶ ሙሉቀን አየሁ በበኩላቸው እንደተናገሩት የባሕር ዳር ከተማ አሁን ለደረሰችበት ዕድገት ስኬት በዚያ ዘመን የነበሩት የመንግስት ኃላፊዎችና የከተማው ማህበረሰብ ዋነኞቹ እንደሆኑ ጠቁመው በአሁኑ ወቅትም ከዚህ በፊት እንደነበረው የበለጠ ለማስቀጠል የከተማው ማህበረሰብም ሆነ መንግስት በኃላፊነት እየሠራ ነው፡፡ ባሕር ዳር ከተማ አፍሪካ ውስጥ ካሉት ምርጥ እና ጽዱ ከተሞች ውስጥ አንዷ እንደሆነች ጠቁመው ለወደፊትም ይህን ስሟን ጠብቃ እንድትቆይ የከተማው አስተዳደርም ሆነ የከተማው ህዝብ የራሱን አስተዋጽኦ ሊደርግ እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡

የ‹አቦካቦት› መጽሐፍ ደራሲ አቶ ያረጋል ገረመው በየዘመኑ የነበሩት ነዋሪዎቿን ከፍተኛ ጥረት አድንቀው ከተማዋ አሁን ለደረሰችበት ደረጃ ስላደረሷት ታሪክ የማይዘነጋቸው ጥሩ ተምሳሌትና ፈርጦች ሲሉ አሞካሽተዋል፡፡ በዘመኑ በነበሩት ነዋሪዎቿ ከፍተኛ ጥረት፣ ረዥሙና ጠመዝማዛው የዓባይ ወንዝ እና በሩቅ ተንጣሎ ሲያዩት ቀልብን የሚማርከው የጣና ሐይቅ በአካባቢው ከተማዋን አቅፈው ለዘላለም መኖር፣ የሩቅ ዘመንን ታሪክ የተጎናጸፉት ገዳማት ለጎብኝዎች ምቹ ሁኔታን መፍጠራቸው፣ በአንድ ወቅት የሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የሲራራ ንግድ ማዕከል ሆና መገኘት እንዲሁም የቀዳማዊ ኃይለስላሴን ቀልብ ለመሳብ በመቻሏ ንጉሱ ለመናገሻ ከተማነት ከመረጧቸው ጥቂት ታዳጊ ከተሞች መካከል ግንባር ቀደም በመሆኗ ከተማዋ አሁን ለደረሰችበት ደረጃ ተጠቃሽ ምክንያቶች መሆናቸውን በመጽሀፉ መካተቱን አቶ ያረጋል ገልጸዋል፡፡ የድሮዋን ‹አቦካቦት› የአሁኗን የጣናዋን ፈርጥ የባሕር ዳር ከተማ ታሪክ ለመጻፍ ከአምስት ዓመት በላይ እንደፈጀባቸውና ታሪኩ ለልጅ ልጅ እንዲሁም እውነተኛ ታሪክን ለአዲሱ ትውልድ ለማስተላለፍ እንደሆነ ደራሲው ጠቁመዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርና ተመራማሪ እንዲሁም በአማራ ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ፎረም ዋና ፀሀፊ ፕሮፌሰር አብይ ይግዛው ስለ መጽሐፉ አጠቃላይ አስተያየት የሰጡ ሲሆን በገለጻቸው ‹አቦካቦት› በቋንቋ አጠቃቀምና በአጠቃላይ በጽሑፉ ይዘት የተዋጣለት ስራ ከመሆኑም በላይ ስለ ባሕር ዳር ታሪክ ምሉዕ የሆነ ጽሑፍ ይዞ የቀረበ የመጀመሪያው ጽሑፍ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

መጽሐፉ ባሕር ዳር ከተማ እንዲህ አሁን በተዋቡ ህንፃዎች፣ ማራኪ የአስፓልት መንገድ እና የከተማዋ መለያ የሆነው ዘምባባ አጊጣ የህዝብ ቀልብ የምትስበው ከዛሬ አንድ መቶ አመት በፊት አንድ ትንሽ መንደር ሆና ጥቂት ሰዎች በግብርና ሥራ ላይ ተመስርተው ይኖሩባት የነበረች እንደነበር፤ ከተማዋ ከትንሽ መንደር ተነስታ አሁን ከደረሰችበት ደረጃ ለመድረስ በርካታ ውጣ ውረዶችን

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# የጎርፍ አደጋን ለመከላከል ...

ከገጽ 4 የዞረ

በሁለተኛው የትራንስፎርሜሽን እና ስትራቴጂክ ዕቅድ የበለጠ ለማሳካት የአምስት ዓመት እቅድ አቅዶ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የአማራ ክልል ጎርፍ ከሚያጠቃቸው ክልሎች አንዱ ሲሆን ይህ ስልጠና በክልሉ ከሚገኙ ጎርፍ ከሚያጠቃቸው አካባቢዎች ከሆኑት ፎገራና ሊቦከምከም ወረዳዎችን እንደማሳያ አድርጎ የሚወሰድ ስልጠና እንደሆነ እና የጎርፍ አደጋው ከተከሰተ በኋላ ችግሩን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል፣ የተግባቦት፣ የንብረት አያያዝና የማስተባበር ሥራው እንዴት መሠራት እንዳለበት መንገድ የሚያሳይ ስልጠና እንደሆነ እና ሰልጣኞችም ከስልጠናው ያገኙትን ዕውቀትና ልምድ በተግባር እንዲያውሉት አቶ አማረ አሳስበዋል፡፡ በመጨረሻም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመሥራት ጽ/ቤቱ ፍላጎት እንዳለው ተናግረዋል፡፡

# The Micro and Macro Contributions...

continued from page 6

like Ethiopia, where community and community based institutions can play a pertinent role in production of goods and services, more so, at the micro - level. The solution lies in localization, democratization and de-bureaucratization of institutions. There is a need for more research in the areas of community empowerment, democracy and citizenship, role of civil society organizations (CSOs) and collaborative networking among the NGOs that implement different development programs and projects. The existing local institutions where members of the society have a central place to make decisions and express their free will can be genuine local institutional innovations.

For a country to escape from the *vicious circlesof poverty* (*to use Nurkse's Phrase*), reconstructingcivil society organizations based on the free will and consent of the community (as clearly observed in *EdirsandEkubs*)seems an alternative paradigmto re-engineer all-rounded transformation. By doing so, it is possible to promote social trust and enable the citizenrydemonstrate commitment to*social change* and *organizational development*. The reconstruction of civil society so that it serves as spheres of public debate, hope for the best, will push democratic deliberation at macro level [regionally or nationally] and academic discourses at micro (university level). If there is deliberative democratic culture, there is political development. Political development, in its turn, enhances socio-economic development. Civil war, political turmoil, sectarianism and other evils can be avoided with the emergence of civilized society, which in turn, is achieved by locally crafted civil society organizations. It is acknowledged that locally crafted civil society organizations has the potential to bring different ideas promoted by different groups into a coherent whole. This is also observed at *Totaw Cafe*. Sometimes, very hot discussionswith divergent views are forwarded by faculty members who are sitting in circles or sometimes in a rectangular form. However, at the end of the discussions, it is common to observe the approval of one central ideaby acclamation.

Though the scope of this article is to share ideas about the importance of civil society organizations in the context of the university, it seems also important to retell its relevance also to the regions in particular and the country in general. For countries, experimenting democracy, it is argued, civil society organizations has the potential to make citizens engage in self-reflection and bring their divergent views into consensus. It is advisable, therefore ,for the government, civil society and private sector to work as partners in the crucial problem areas confronted by the society. Without a strong civil society to nourish engaged citizens, it has been stated by some researchers, corruption prevails rampantly. And , it is also declared that the bureaucracy will suffer from procrastination of services. Still, without strong civil society organizations in a given country, it is remarkably stressed thatcitizens are reduced to mere antagonists or turn into ungrateful clients of government services. With a vibrant civil society which is endowed with good *social capital*, however, it is declared that jointly owned common resources (public properties) are responsibly managed. Furthermore, the problem of corruption can be tackledand rational self-interested (free-rider) individuals can be challenged; and thus, it has been claimed by researchers,minimizing poverty incidences can be realized though eradication of it will still demand***holistic human development (HHD)****; that is, a change in both the* ***Hardware*** *[ability to change our knowledge into practice] and the* ***Software*** *(attitudinal change for the good; not, for the bad].*

Very recently, it is also learnt that market- state endeavors have overwhelmed the economy with many public sector enterprises divesting and opening up to private entrepreneurs. Nevertheless, domestic market regulation has its own malfunctions. Here, it seems importance to remember the variation of prices of goods in a single town/city. Genuinely, prices affect production since they determine relative profitability and economic incentives. If the price at which the output can be sold is attractive and a profit can be made, or the relationship between output prices and input costs becomes favorable, suppliers will have the incentive to produce more. But, sometimes, the opposite is true and suppliers lack the incentive to increase their produce. There has been successful accomplishments between state and civil society, especially, in the areas of conflict resolution, resource management and rural development programs quite recently. However, civil society organizations must be motivated to enter into the local market functioning boldly so that suppliers can be beneficial of their produce. It is of paramount importance to the civil society to fruitfully associate itself with the state as well as the market tobenefit the larger sections of society and to adjust instabilities of prices of goods for collective well-being of society. In a similar way, the state should pave the way for civil society organizational structures and functioning in accordance with the willing engagement of the community/society.

Particularly, since the 1980s, third sector endeavors have found favor with the theoretical and applied developments in public administration especially under the command of policy-directors (World Bank and IMF). It is significant to recall the introduction of governance which is linked to international aid conditionality to developing countries like ours Ethiopia [refer the previous article by this writer on revisiting governance].

The public choice approach and now the New Public Management (NPM) attempts to provide alternatives to bureaucratic hegemony. Unfortunately, however, the public choice perspective seeks to reduce individuals to utility maximizers or *rent- seekers* to use Political Economist David Ricardo's phrase. This is because, it does not provide the mechanism for arriving at a collective general interest. The underlying principles of the New Public Management (NPM) treats the citizens as mere clients and consumers. The pluralistic, communitarian, New Public Administration (NPA) and Network Agency perspectives give due regard to community, non-bureaucratic institutions and values, but do not attempt to develop the idea of autonomous, self- reflexive, human and conscientious civil society with accent on ***Genuine Public Interest*** **(GPI).***What is required, therefore, is a third paradigm that treats citizens as equal partners in development and equality of opportunity with due regard to goals of equity and social justice.* The civil society organizations must be strengthened and concerned more with rectifying the malfunctioning of state and market through empowerment of the rural and urban poor in particular and the Ethiopian societyin general.

The rich experiences of *Edirs* and *Ekubs*and beginnings of successful civil society organization like professional associations(e.g. teachers' & Chauffeur's Association in BDU), women's groups, micro- credit association, farmer cooperatives (like Merkeb Union), trade unions and chambers, local credit networks, youth forums,and canteens (*like Totaw cafe which provide services with fair prices* ) should strike their roots in every part of the country so as to equally distribute social and economic benefits to the society on the one hand and enhance the culture of discourses and deliberations on the other.

In wanting to open up new democratic terrain, the core justificatory principle is that major arenas of social, economic and political power... power over people's lives and power that shapes the life of society itself... should be harnessed into a doctrine of democratic responsibility. This is a responsibility that acknowledges a framework of obligation and accountability, recognizes a range of legitimate stakeholders and seeks ways in which these stakeholders can have an effective voice. An approach of this kind will not be impressed by attempts to construct iron walls between "public" and "private" centers of power, but will instead want to apply the doctrine of responsibility to both, as remarked by Benjamin Barber (1996) in his article "*Three Challenges to Reinventing Democracy*". As reputable political theorist, Barber argues for a renewed focus on civil society and engaged citizenship as tools

continued on page 14

## ፈጣን መረጃ

### በ2008 የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ክፍሎች የምርምር ፕሮጀክቶች

| የምርምር ማዕከሉ ስም | ከ2008 በፊት የተጀመሩና በሂደት ላይ ያሉ ብዛት | በ2008 አዲስ ሊሰሩ የታቀዱት ብዛት | የተቋረጡ | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| ሳይንስ ኮሌጅ | 11 | 24 | -- | 35 |
| ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | 4 | 33 | - | 37 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሞክስ ኮሌጅ | --- | 31 | -- | 31 |
| ግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ | --- | 16 | -- | 16 |
| ትምህርትና ስነባህርይ ኮሌጅ | --- | 14 | -- | 14 |
| ሶሻል ሳይንስ ፋካልቲ | --- | 11 | -- | 11 |
| ሂዩማኒቲስ ፋካልቲ | --- | 8 | --- | 8 |
| መሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት | --- | 7 | 2 | 9 |
| ህግ ትምህርት ቤት | --- | 4 | --- | 4 |
| ስፖርት አካዳሚ | - | 4 | --- | 4 |
| ድምር | 15 | 152 | 2 | 169 |

# «ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው»

በአምሳሉ ጥላሁን

በየትኛውም ማህበረሰብ እና ሀይማኖት ተከታዮች ዘንድ በዓላት ትርጉም አላቸው፡፡ በበዓላት ጊዜ የቅርብ ዘመድንና ጓደኛን በመሰብሰብ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት ከፍተኛ ደስታን ይሰጣል፡፡ በከተማ አካባቢ ለቅርብ ሰዎቻችን ስጦታ መስጠት እየተለመደ መጥቷል፡፡ ነገር ግን ጐዳና ላይ ወድቀው ደጋፊ ለሌላቸው ወገኖቻችን አዲስ ልብስ ገዝተን በዓሉን በደስታ እንዲያከብሩ ማድረግ ባንችልም ቤት ያፈራውን ምግብም ሆነ መጠጥ በመስጠት በጋራ ማክበር እንደምንችል አምናለሁ፡፡

የገና በዓል በሀገራችን ከሚከበሩ ሃይማኖታዊ በዓላት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በዓሉ በከተማም ሆነ በገጠር በተለየ ሁኔታ ይከበራል፡፡ «በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ» የሚለውን ባሕል እንደሚያስረዳው በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች ወንዶች በጋራ ያለምንም ልዩነት ወደ ሜዳ በመውጣት የገና ጨዋታን ያካሂዳሉ፤ በመጨረሻም በጋራ እየጨፈሩ በየቤቱ እየዞሩ ምርቃት ይቀበላሉ፡፡ በእድሜያቸው የገፉት ደግሞ በጋራ በመሆን ለበዓሉ ከተዘጋጀው ምግብም ሆነ መጠጥ እየጠጡ በደስታና በሐሴት ያከብሩታል፡፡ አንዱ ላንዱ ይተሳሰባል፡፡ ወደ ከተማ ስንመጣ አብሮ መብላትም ሆነ መጠጣት የተለመደ ቢሆንም ጧሪ ላጡ አዛውንቶችም ሆነ ወላጅ ላጡ ህፃናት እንደ ገጠሩ ማህበረሰብ የመርዳት ባሕላችን ግን ሊፈተሽ ይገባል እላለሁ፡፡

አብሮ የመብላትና አብሮ የመጠጣት ትርጉም የገባቸው የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የዋናው ግቢ፣ የቴክኖሎጂ ግቢ እና የይባብ ግቢ የመደበኛው መርኃ ግብር ተማሪዎች RDL እና KHA ክበባትን በማቋቋም በከተማው ውስጥ የሚገኙ አዛውንቶችና ህፃናትን እየረዱ ይገኛሉ፡፡ የትምህርት ጊዜያቸውን እንዳይሻማ ፕሮግራም በማውጣት እንዲሁም በመተካካት በየቀኑ ልዩ ልዩ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ክበባቱ «ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው» የሚለውን መፈክር በማንገብ በባሕር ዳር ከተማ ውስጥ የሚገኙ ጧሪ እና ደጋፊ ያጡ አዛውንቶችንና ህፃናትን በመሰብሰብ የገና በዓልን በደማቅ ሁኔታ በጋራ አክብረዋል፡፡

እነዚህ ክበባት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከበሩ በዓላትን ምክንያት በማድረግ የበጎ አድራጎት ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡ ይህን የተለመደውን የበጎ አድራጐት ስራቸውን ሲያከናውኑ በተለይ ጧሪ እና ረዳት የሌላቸውን አዛውንቶችንና ህፃናትን በመሰብሰብ በዓላትን ሲያከብሩ ለተመለከተ ሰው ከፍተኛ ትርጉምና መልዕክት ያለው ስሜት ይሰጣል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በዓላትን ከቤተሰብ ርቀው የሚያከብሩ አይመስሉም፡፡ በፍጹም ደስታ ውስጥ ናቸው፡፡ ተማሪዎቹ አዛውንቶችንና ህፃናትን ለማስተናገድ ወዲህና ወዲያ ሲጣደፉ የተመለከተ ሰው እውነትም ለህዝብና ለወገን የቆሙ መሆናቸውን ይመሰክራል፡፡ እንደ እኔ ጠጋ ብሎ ስራቸውን የተመለከተ ደግሞ «ከክፉ አይን ያውጣችሁ» ብሎ ከመመረቅ ወደ ኋላ አይልም፡፡ የሰው ልጅ እንዲህ ያለ መልካም ሥራ ቢሰራ ለህሊና ትልቅ ደስታ እንዲሁም እርካታ እንደሚሰጥ ከተረዳን መረዳዳትን ባሕላችን ሆኖ እንዲቀጥልና የማንነታችን መገለጫ ማድረግ እንችላለን፡፡

ከእነዚህ በጎ አድራጊዎች መረዳት የቻልኩት ሰውን ለመርዳት የግድ ሀብትና ንብረት አያስፈልግም - በጎ ህሊናና ሀሳብ እንጂ፡፡ በጎ ሃሳብ የሌለበት ድርጊት መጨረሻው ቀና አይሆንም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ለበጎ አድራጎት የሀብትና ንብረት እጥረት እንዲሁም የመርዳት ዘዴው አልገባን ብሎን ወደ ጐን እንሸሻለን፡፡ ይህ ዘይቤ የገባቸው እነዚህ ተማሪዎች ግን ችግር ውስጥ ያሉ የማሕበረሰብ አካላትን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው ብለው ተነስተዋል፡፡ የበዓሉ አስተባባሪዎች የሆኑት የቴክኖሎጂ ግቢ የኤሌክትሪክ ምህንድስና ተማሪ ረዴት ከፈለኝ፣ የዋናው ግቢ የቱሪዝምና የሆቴል ማኔጅመንት ተማሪ በላይነህ ዘሪሁን እንዲሁም የይባብ ግቢ የሕግ ተማሪ እዮኤል ሰለሞን እንደገለጹልኝ ክበባቱ በከተማው ውስጥ የሚገኙ አዛውንቶችና ህፃናትን ብቻ መርዳት ሳይሆን በተለያዩ ሱሶች የተጠመዱ ወጣቶችን ከሱስ እንዲወጡ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ መሆናቸውን እንዲሁም ወደፊትም ክበባቱን ሀገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በማድረግ የበጎ አድራጎት ስራቸውን በይበልጥ ለማጠናከር እየሰሩ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡ እነዚህ የነገ ሀገር ተረካቢ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላደረጉላቸው ድጋፍና ትኩረት ትልቅ ደስታ እንደፈጠረላቸው ከበዓሉ ታዳሚዎች ለመረዳት ችያለሁ፡፡

> **ከእነዚህ በጎ አድራጊዎች መረዳት የቻልኩት ሰውን ለመርዳት የግድ ሀብትና ንብረት አያስፈልግም - በጎ ህሊናና ሀሳብ እንጂ፡፡**

ነገር ግን ወርቅ በእሳት እንደሚፈተነው ሁሉ ይህን የበጎ አድራጎት ስራዎች ለመስራት ተማሪዎቹ ብዙ ውጣ ውረዶችን ማለፍ ግድ ነበረባቸው፡፡ ግን በመልካም ሁኔታ አልፈውታል፡፡ ነገ ከዚህ የበለጠ ስራ እንዲሰሩ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ከጐናቸው መቆም እንዳለበት እውን ነው፡፡ እያንዳንዳችን የራሳችንን ድርሻን መወጣት እንዳለብን ማመን አለብን፡፡ የተቸገረን አይቶ ከንፈር መምጠት ብቻ ሳይሆን እኔ ምን ማድረግ አለብኝ ብሎ እራስን መጠየቅ ትልቅ ኃላፊነት መሆኑን ተገንዝበን እራሳችንን እንፈትሽ!

# The Micro and Macro Contributions ...

**continued from page 13**

for building effective democracy, particularly in the post-Cold War world. This writer would also like to call a renewed attention to civil society organizations by researchers, policy makers, and the Ethiopian community.

Thus, this new thinking should not be seen as a shift in power from the state to the civil society, but rather as the natural evolution of the relationship between those *Who Govern and those Who are Governed*. In other words, this provides golden opportunities for government to learn to govern better through paying attention tovoices of the people; and citizens will learn to be better citizens through exposure to the regular rules and disciplined practices of civil society organizations. Similarly, the private sector has a large stake in the expansion of civil society since civil order fosters economic growth. The synergies arising out of the emerging relations between the state, private sectorand civil society organizations must thus be put to practical use. Hopefully, at micro level, therefore, this should be wider intervention area to transform institutions (like BDU) to critical discourse, research and innovation. Likewise, at macro level, it should also be critical area of policy intervention to transform regional states and Ethiopia to both economic development and democratic deliberation.

To conclude, community-based institutions have become more pertinent with the withdrawal of the state from certain areas and the influx of markets at the national and international levels. To understand the transformative role of the civil society organizations; hence, its undertones have to go beyond its connection with NGOs and other more profit-oriented community based organizations. Other indicators of civility have to be thought. For instance, establishing a well-informed and well-informing mass media could bring in the necessary change. Establishing canteens like *Tota cafe* near the working environment for both teachers and students has the potential of serving as spheres of public debate.The promising advantages ofestablishing different spheres of public debate at *local, regional, and nationallevels*should be fully reconnoitered.

Civil society organizations, on their behalf, must have a specific purpose, a clear-cut agenda, an organized modus-operandi, an autonomous functioning mechanism and a self-reflexive evaluation capacity. It should be recognized that the civil society organizations do not assume anti-democratic, fundamentalist and oppressive roles. A clarity on their boundaries, access, roles and functions is a precondition for achieving their vision and mission. A country rooted in strong civil society traditions could ensure that all the prerequisites of good governance; namely, equity and inclusiveness, social justice, efficiency and effectiveness, transparency, accountability, access to information, participation and responsiveness are realized. This is possible only if conditions for a mutually advantageous existence of state, market and community-based organizations are nurtured and sustained in the present globalization context. Cooperativeness among the actors, can make the implementation of public policy effective. Failure to cooperate among the actors, no doubt, is *Bowling Alone* to use Putnam's phrase, which will; ultimately, lead to social and economic down turn.All in all, the scientific community of BDU has to think of conducting further research in this thematic focus!

***Remark***:
This writer used the name *Totaw Cafe* assuming that it gets the ***consent*** of the community of the main campus in BDU. In the writer's opinion ,whatever implication does it have and as far as it gets the consent of the community, its name is ok. What is important is the quality of the service it provides to the community!

To follow the latest news about BDU, check out our website:- **http://www.bduinfo63@bdu.edu.et or http://www.bdu.edu.et**

facebook page:- **www.facebook.com/bdu-ethiopia**

# Ethiopia Climate Innovation Center

Infodev's Climate Technology program's flagship initiative is a network of climate Innovation Centers ( CICs) which will accelerate the development, deployment and transfer of locally relevant climate technologies in developing countries. The Ethiopia Climate Innovation Center (ECIC) was launchedunder this initiativeon March 27,2014. Seven other CICs are being established, in the Kenya, Caribbean, Ghana, India, Morocco, South Africa, and Vietnam.

The ECIC is strongly supported by the Ethiopian government and is implemented through a four member consortium led by the Horn of Africa Regional Environmental Center and Network (HoA-REC&N).

The ECIC provides a holistic set of early-stage financing, business support and capacity building services to the Ethiopian private sector, including women and rurally based entrepreneurs and business owners, working to develop, launch and grow innovative climate technology ventures that promote Ethiopia's climate resilience and green growth.

The ECIC provides domestic enterprises with a broad range of services including:

- Financing through proof-of-concept grants (up to 1 million Birr) as well as investment facilitation at more advanced stages.
- Business advisory and training through mentorship, networking, seminars, and other services that build professional expertise.
- Access to market information, local technology information, access to facilities and regional centers.
- Access to policy support through hosting dialogues with government, researching trends and documenting best practices for SME and climate technology regulation.
- Promoting business opportunities for women and outreach on climate innovation.

In collaboration with local stakeholders five thematic areas were identified as specific climate technology sectors that the ECIC would support. The thematic areas of focus for the center are: Sustainable Agribusiness, Bio-fuels, & Bio-mass, Transportation technologies, Micro-Hydropower and Energy Efficiency.

The ECIC accepts climate technology entrepreneurs as clients that have access to the above services through its Proof of Concept (POC) competition. The ECIC had conducted two rounds of POC competition and accepted 39 clients. The third round of POC competition is underway with 33 semi-finalists selected.

To ensure that climate technology entrepreneurs from the regions obtain support and contribute towards the adaptation and mitigation of the effects of climate change as well as to job creation, the ECIC launched its first outreach center onthe 11th June 2015 in the Amhara Regional State, Bahir Dar city. This ECIC outreach center was opened in collaboration withBahir Dar University. The main objective of the Bahir Dar Outreach center is to inform regional stakeholders, parterns, potential entrepreneurs and entreperneurs about the services of the ECIC and build collaborative relationships. The Outreach Center also works to support the region's climate technology clients of the ECIC.

The Bahir Dar Outreach Center's office is located within Bahir Dar University Wisdom tower 4 th floor room 3.

ECIC Amhara Region Outreach Cente

# የባሕር ዳር ከተማን ታሪክ ...

ከገጽ 12 የዞረ

እንዳሳለፈች እንዲሁም ከተማዋ ታሪኳን በጽሑፍ የሚያሰፍሩ የውጭ አገር ዜጎች እና የሀገር ውስጥ የታሪክ ምሁራን ከከተሙባት ጊዜ ጀምሮ የክልል ርዕሰ ከተማ እስከሆነችበት ጊዜ ድረስ በርካታ የአመራር አካላት በታሪክ ቅብብሎሽና የሥራ ተነሳሽነት እንዳስተዳደሯት ያስነበበናል፡፡

ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ለባሕር ዳር በነበራቸው ከፍተኛ ፍቅር ገና መንደር እያለች ወደ ከተማዋ በመምጣት ጫካ እየጣሱ ዱር እያስመነጠሩ አካባቢውን በተደጋጋሚ እየጎበኙ ለመመለሳቸው በርካታ ማስረጃዎች እንደሚገኙ እና ንጉሱ በነበራቸው አዲስ የመናገሻ ከተማ መመሥረት ፍላጎት በተለያዩ ጊዜያት አካባቢውን እንዲያጠኑ ከውጭ አገር የመሀንዲሶች ቡድን በማስመጣት ወደ ከተማዋ እየላኩ የጥናት ሪፖርት እንዲያቀርቡላቸው ያደረጉ ሲሆን በተለይ በዶክተር ጉንተር የተጠናውን ማስተር ፕላን ተመርጦ ከተማዋ ውብ ገጽታ እንድትላበስ ሥራውን አስጀምረዋል፡፡ ሆኖም ግን ከተማዋን በማስተር ፕላኑ መሠረት ለማስገንባት የገንዘብ፣ የተደራጀ የሰው ኃይል፣ ግንባታ መገልገያ መሳሪዎች እጥረት እንዲሁም የነዋሪው ህብረተሰብ የስነ-ልቦና ዝግጅት ፈተናዎች እንደነበሩ መጽሀፉ ያነሳል፡፡

## የኔ ጀግና

ጊዜው ተመችቶት ወንበሩን አግኝቶ
አጋጣሚው ሁሉ ለእርሱ ተመቻችቶ
ያሻውን ለማድረግ ያሻውን ለማፈስ
አንዱን ለመግንባት ሌላውን ለማፍረስ
እማኝ በሌለበት ዳናውን አጥፍቶ
ብዙ ለመሰብሰብ ሁኔታ ተቃንቶ
በትከሻው ታምኖ እህቱን ወንድሙን
አክስት አጎቶቹን ዘመድ አጋሮቹን
እየሰባሰበ ጎጡን ከያለበት
ሥፍራ መስጠት ሲችል በተገኘው ክፍተት
እርሱ ግን ……
ለህሊናው አድሮ እውነትን ተላብሶ
ሀገሩን ኢትዮጵያን በልቡ አንግሶ
ሸፍጥና ምዝበራን እጅግ ተፀይፎ
እራሱን ለሌሎች ከተሰጠ ታልፎ
ጊዜውን ወንበሩን ለህዝቦች አዳራ ከተጠቀመበት
አርዕያ ለትውልድ ይህ ነው ጀግና ማለት
ለኢትዮጵያ ህዳሴ የታሪክ ባለቤት (ወደፊት)፡፡

በደስታ ተከስተ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀጥታ አገልግሎት

# ፎቶ ማህደር





የጎርፍ አደጋን ለመከላከል የሚያስችል የተግባር ስልጠና ሲሰጥ

ለዝርርዝሩ ገጽ 4ን ይመልከቱ











ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከ2ኛ ፖሊስ ጣቢያ ጋር በመተባበር ያሰለጠናቸው የተማሪ ትራፊክ ፖሊሶች የምርቃ ስነ ስርዓት

ኀህ ማተሚያ ቤት ታተመ